fetena.net : Ethiopian online exams and textbook





አማርኛ

እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ
የተማሪ መጽሐፍ
፪(2)ኛ ክፍል

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የትምህርት ሚኒስቴር

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ
በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የተስማማ

አስማምቶ አዘጋጆች

ሞላ መኮንን አበራ
ይርገዱ ተድላ በየነ

የጥራት ክትትል

ፍሬህይወት አሠፋ ከበደ



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የትምህርት ሚኒስቴር

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው ከአሜሪካ ህዝብ በአሜሪካ ዓለምዓቀፍ የልማት ድርጅት /United States Agency for International Development (USAID)/ በኩል በተገኘው የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ፣ በትምህርት ሚኒስቴር፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮና READ TA ፕሮጀክት ትብብር ሲሆን የማስማማቱ ስራ የተከናወነው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ሆኖ የህትመቱ ወጪ በሁለተኛው የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፕሮግራም /General Education Quality Improvement Program (GEQIP) II/ ተሸፍኗል።

የመጽሐፉ ህጋዊ የቅጂ ባለቤት ©2007 ዓ.ም. በኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ነው።

ISBN: 978-99944-2-359-0

ማውጫ

ጠቃሚ መረጃ ለወላጆች v

1ኛ ሳምንት 1

2ኛ ሳምንት 6

3ኛ ሳምንት 12

4ኛ ሳምንት 18

5ኛ ሳምንት 24

6ኛ ሳምንት 29

7ኛ ሳምንት 34

8ኛ ሳምንት 38

9ኛ ሳምንት 42

10ኛ ሳምንት 46

11ኛ ሳምንት 50

12ኛ ሳምንት 54

13ኛ ሳምንት 59

14ኛ ሳምንት 63

15ኛ ሳምንት 67

16ኛ ሳምንት 71
17ኛ ሳምንት 75
18ኛ ሳምንት 79
19ኛ ሳምንት 83
20ኛ ሳምንት 87
21ኛ ሳምንት 91
22ኛ ሳምንት 95
23ኛ ሳምንት 99
24ኛ ሳምንት 103
25ኛ ሳምንት 107
26ኛ ሳምንት 112
27ኛ ሳምንት 116
28ኛ ሳምንት 120
29ኛ ሳምንት 124
30ኛ ሳምንት 128

ጠቃሚ መረጃ ለወላጆች

መግቢያ

ይህ መጽሐፍ ሕጻናትን በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የማዳመጥና የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ችሎታ ለማበልፀግ ተሻሽሎ የተዘጋጀው የአፍ መፍቻ ቋንቋ መርሃትምህርት አካል ነው። መጽሐፉም ሲዘጋጅ መነሻ ያደረገው ሕጻናት ማንበብና መጻፍ እንዴት እንደሚማሩ የሚረዱ ጥናቶችንና የአማርኛ ቋንቋን መሠረታዊ ባህርያት ነው።

የዚህ የአፍመፍቻ ቋንቋ ሥርዓተ ትምህርትና መርሃትምህርት መሠረታዊ መርሆች የሚከተሉት ናቸው።

1. ሕጻናት እንግዳ ቃላትን ለማንበብና ቃላትን በተገቢ የፊደላት አሰዳደር ለመጻፍ፣ የቋንቋው ፊደላት የሚወክሏቸውን ድምፆች መማር ይጠበቅባቸዋል፤
2. ሕጻናት በተቻለ መጠን በቅድሚያ ቃላትን ቀጥሎም ዓረፍተ ነገሮችን ማንበብ አለባቸው፤ እነዚህ ቃላትና ዓረፍተ ነገሮች በተማሯቸው ፊደላት የተመሠረቱ መሆን አለባቸው፤

3. ሕጻናት በፍጥነት፣ በትክክልና ያለችግር እንዲያነቡና ራሳቸውን በንግግርም ሆነ በጽሑፍ በትክክልና በግልጽ ቋንቋ ለመግለጽ እንዲችሉ የማንበብና የመጻፍ በርካታ ተከታታይ ልምምዶች ማድረግ አለባቸው፤

4. ሕጻናት አዳዲስ ቃላትን ሲያዳምጡና ሲያነቡ የቃላቱንም ፍቺ አብረው መማር አለባቸው፤ በዚህም የሚያዳምጡትንና የሚያነቡትን መረዳት ይችላሉ፤ ቋንቋቸውንም በንግግርና በጽሑፍ በአግባቡ ይጠቀሙበታል፤

5. ሕጻናቱ ተረቶችን/ታሪኮችንና ሌሎች ጽሑፎችን ሲያነቡ ሀሳቡን ለመረዳት ይችሉ ዘንድ የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ክሂሎችን ማዳበር አለባቸው።

ልጆችዎን በቤት ውስጥ ይርዱ!

ወላጆች ልጆቻቸው ማንበብና መጻፍ እንዲማሩና ቋንቋውን በአግባቡ መጠቀም እንዲችሉ በቤት ውስጥ መርዳት ከሚችሉባቸው አጠቃላይ መንገዶች የሚከተሉት ይጠቀሳሉ።

1. ለልጆችዎ ተረቶችን/ታሪኮችን ይንገሯቸው።
2. ልጆችዎ ተረቶችን/ታሪኮችን እንዲናገሩ ይጠይቋቸው።
3. ልጆችዎን እርስዎ ስላነበቡላቸው ወይም ስለነገሯቸው ተረቶች/ታሪኮች ያሏቸውን አስተያየቶች ለሌሎቻችሁ እንዲያካፍሉ ይጠይቋቸው። ይህም የአዳምጠ፣ የአንብቦ መረዳትና ጥሩ የመናገር ክሂሎቻቸውን እንዲያዳብሩ ያግዛቸዋል።
4. ለልጆችዎ ራስዎ ወይም ሌሎች ተረት/ታሪክ እንዲያነቡላቸው ያድርጉ፤ ይህም ለልጆቹ የሚያነቡትን ጽሑፍ በሌላ ሰው ሲነበብ ምን እንደሚመስል የማዳመጥ መልካም አጋጣሚ ይፈጥርላቸዋል፤ በራሳቸውም ለማንበብም ፍላጎት ያሳድርባቸዋል። ከልጆቹም ጋር ስለምታነቡት ጽሑፍ ተወያዩ።
5. በሚያውቋቸው (በተማሯቸው) ፊደላት የተመሠረቱ ቃላትን እንዲያነቡ ያድርጓቸው።
6. በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ ጽሑፎችን ወይም ሌሎች ለደረጃቸው የሚመጥኑ ቀላል ጽሑፎችን እንዲያነቡ ያበረታቷቸው። ለማንበብ የሚቸገሩባቸውን ቃላትና ዓረፍተነገሮች እንዲያነቡ ያግዟቸው።
7. ልጆችዎ በራሳቸው እንዲያነቡ ያበረታቷቸው።
8. ልጆችዎ ለቤተሰብ አባላት ወይም ለጓደኞቻቸው በራሳቸው ማስታወሻ እንዲጽፉ ያበረታቷቸው።

የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ

የትምህርቱ ክፍሎች (ይዘቶች)

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እያንዳንዱ ትምህርት በምልክት የተጠቆሙ ክፍሎች አሉት። ጥቂት ክፍሎች በተወሰኑ ትምህርቶች ውስጥ ብቻ የሚከሰቱ ቢሆንም፣ ብዙዎቹ ክፍሎች ግን በእያንዳንዱ ትምህርት ውስጥ ይገኛሉ።



የማዳመጥ ምንባብ

ይህ ክፍል የሚያተኩረው በአዳምጦ መረዳት ላይ ነው።

በክፍል ውስጥ ልጆቹ፦

- በመምህራቸው የሚነበበውን ተረት/ታሪክ ወይም መረጃ ሰጪ ጽሑፍ ያዳምጣሉ፤
- ርዕሱንና ሥዕሎችን በመመልከት ምንባቡ ስለምን እንደሆነ ይገምታሉ/ያስባሉ፤
- ካዳመጡት ምንባብ የወጡ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፤
- በምንባቡ ላይ ይወያያሉ።

ወላጆች በቤት ውስጥ ልጆችን ለመርዳት፣

- ልጆች ስለምንባቡ የሚያስታውሱትን እንዲናገሩ ይጠይቋቸው፤ ሥዕሎቹ ተረቶቹን/ታሪኮቹን ለማስታወስ ሊረዷቸው ይችላሉ።



አዲስ ወይም ተተኳሪ ፊደል

ይህ ክፍል በተተኳሪ ፊደላት ላይ የሚያተኩር ነው። ይህም የሚገኘው በትምህርት ዓመቱ ባሉት የመጀመሪያ አምስት ሳምንታት ውስጥ ብቻ ነው።

በክፍል ውስጥ ልጆቹ፡-

- ከዚህ ቀደም ያልተማሯቸውን ሞክሼና ውስብስብ ፊደላት ይማራሉ፤
- ፊደሎች በቃላት ውስጥ ያላቸውን ንበት (ምን ዓይነት ድምጽ እንዳላቸው) ይማራሉ፤
- በእያንዳንዱ ፊደል የሚጀምሩ ወይም የሚጨርሱ ቃላትን ለመለየት ይችላሉ፤
- ፊደላቱን በማየት የሚወክሏቸውን ድምፆች መጥራት ይለማመዳሉ፤
- የተማሯቸውን ፊደላት ይለማመዳሉ።

ወላጆች በቤት ውስጥ ልጆችን ለመርዳት፡-

- ሕጻናቱ ቀደም ብለው የተማሯቸውን ፊደላት መመልከት ይችላሉ፤
- ሕጻናቱን ፊደሎቹ ማን ማን እንደሆኑና የሚወክሏቸውም ድምፆች የትኞቹ እንደሆኑ ይጠይቋቸው፤
- በተለያዩ ፊደሎች የሚጀምሩ ቃላትን አስበው እንዲነግሩዎ መጠየቅ ይችላሉ።



ማጣመር/መነጠል

ይህ ክፍል ቃላትን በማንበብና ወደተለያዩ ክፍሎች በመነጠል ወይም በማጣመር ላይ ስለሚያተኩር፣ ልጆቹ ቃላቱን እንዲያነቡና በተገቢ የፊደል አሰዳደር ሥርዓት እንዲጽፉ ያግዛቸዋል።

በክፍል ውስጥ ልጆቹ፡-

- ቃላትን "ማጣመር"፡- ቃላቱ የተመሠረቱባቸውን ፊደሎች ወይም የቃላቱን የተነጣጠሉ አሀዶች ለየብቻ ያነባሉ፤ መልሰውም አንድ ላይ ይሏቸዋል፤
- ቃላትን "መነጠል"፡- ቃላቱን ያነባሉ፤ ቀጥለውም ወደፊደላቱ ወይም ወደአነስተኛ አሀዶች ይነጣጥላሉ፤
- ፍቺ ያላቸውን የቃላቱን አሀዶች (ቅጥያዎችን) ለይተው ያነባሉ።

ወላጆች በቤት ውስጥ ልጆችን ለመርዳት፣

- ልጆችን የቃላቱን ፊደሎች ወይም አሃዶች እንዴት እንደሚያጣምሩና እንደሚነጥሉ ይጠይቋቸው። ለልጆቹ ይሄ ጠቃሚ ልምምድ ነው።



ግለንባብ

ይህ ክፍል ሕጻናቱ አዳዲስ ቃላትንና ተዘውታሪ ቃላትን ማንበብ እንዲችሉ ዓረፍተነገሮችን፣ አጫጭር ተረቶችን/ታሪኮችን ወይም መረጃ ሰጪ ምንባቦችን እንዲያነቡ በማድረግ ላይ ያተኩራል። ከዚህ በተጨማሪም በአንብቦ መረዳትም ላይ ያተኩራል።

በክፍል ውስጥ ልጆቹ፡-

- ግለንባቡን ያነባሉ፤
- ከምንባብ የወጡ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፤
- በግለንባቡ ላይ ይወያያሉ፤
- ስለምንባቡ በደረጃቸው ይጽፋሉ።

ወላጆች በቤት ውስጥ ልጆችን ለመርዳት፡-

- የዕለቱን ግለንባብ ይመልከቱና ልጆቹ እንዲያነቡ ይጠይቋቸው፤
- የቀደሙ ግለንባቦችን ይመልከቱና እንዲያነቡልዎ ይጠይቋቸው፤
- ልጆችዎ በግለንባቡ ውስጥ ለማንበብ የሚቸገሩባቸው ማናቸውም ቃላት ካሉ ቃላቱን እንዲለዩዋቸውና እንዲያነቧቸው ያበረታቷቸው፤
- ልጆችዎ ግለንባቡን መውደድ አለመውዳቸውንና ለምን እንደወደዱት ወይም እንዳልወደዱት ይጠይቋቸው።

ቃላት

ይህ ክፍል አዳዲስ ቃላትን በመማርና በመጠቀም ላይ ያተኩራል።

በክፍል ውስጥ ልጆቹ፡-

- ከመምህራቸውና ከሚያዳምጡት ምንባብ አዳዲስ ቃላትን ይማራሉ፤
- አዳዲስ ቃላትን ከሥዕሎች ወይም ፍቻቸው ጋር ያዛምዳሉ፤
- ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ይሰጣሉ፤
- ቃላቱን በዓረፍተነገር ውስጥ መጠቀም ይለማመዳሉ።

ወላጆች በቤት ውስጥ ልጆችን ለመርዳት፣

- ልጆችዎ ቀደም ሲል በተማሯቸው ትምህርቶች ውስጥ ያሉ ሥዕሎችን ተመልክተው በሥዕሎቹ የተወከሉትን ቃላት እንዲገልጹ ይጠይቋቸው።
- ልጆችዎ ስለተማሯቸው ቃላት እንዲነግሩዎ ይጠይቋቸው።



መጻፍ

ይህ ክፍል ፊደላትንና ቃላትን በመጻፍ፣ እንዲሁም ሀሳባቸውን በሥዕልና/ወይም በቃላት በመግለጽ ላይ ያተኩራል።

በክፍል ውስጥ ልጆቹ፡-

- ፊደላትን መጻፍ ይለማመዳሉ፤
- በተማሯቸው ፊደላት ቃላትን ይጽፋሉ፤
- ቃላትን በተገቢ የፊደላት አሰዳደር መጻፍ ይለማመዳሉ፤
- አጫጭር የቃል ጽሕፈትና የፊደል አሰዳደር መከራዎች ይወስዳሉ፤
- ሃሳባቸውንና ግንዛቤያቸውን ለሌሎች ለማካፈል ዓረፍተነገሮችን ይጽፋሉ።

ወላጆች በቤት ውስጥ ልጆችን ለመርዳት፣

- ልጆችዎ የእጅ ጽሕፈታቸውን እንዲያሻሽሉ ፊደላትንና ቃላትን እንዲገለብጡ ይጠይቋቸው።
- ቃላትን በተገቢ የፊደል አሰዳደር ሥርዓት በጽሑፍ እንዲለማመዱ ያድርጉ።
- ልጆችዎ በሚሳሳቱበት ጊዜ ያበረታቷቸው፤
- ልጆችዎ አጫጭር ዓረፍተነገሮች እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፤ ይህም ለቤተሰብ አባላት ወይም ለጓደኞች አጫጭር ማስታወሻዎች እንዲጽፉ በማለማመድ ሊተገበር ይችላል።

1ኛ ሣምንት

1ኛ ቀን

ማዳመጥ

የልብስ ዓይነቶችና ቀለማቸው



ቃላት

በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ።

ምሳሌ:- ኮት → መምህሩ ኮት ለበሱ።

1. ቀሚስ
2. ጋቢ
3. ቁምጣ
4. ሸሚዝ

ሞክሼ ፊደላት

ሀ	ሐ	ጎ	ኸ

ፊደላቱን ዓፉና አንብቡ።

ሀ	ሁ	ሂ	ሃ	ሄ	ህ	ሆ
ሐ	ሑ	ሒ	ሓ	ሔ	ሕ	ሖ

ጎ	ጉ	ጊ	ጋ	ጌ	ግ	ጐ
ኸ	ኹ	ኺ	ካ	ኼ	ክ	ኾ

ማጣመር

አጣምራችሁ ፃፉና ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

ሀ-ብ-ት	ሐ-ብ-ት	ኀ-ብ-ት
ህ-ል-ም	ሕ-ል-ም	ኅ-ል-ም

ግለንባብ

የአበባ አዳዲስ ልብሶች



አበባ ልብስዋ አልቆባታል። ከአባትዋ ጋር ወደገበያ ሄደች። ወደሀፃናት ልብስ ሱቅ ገቡ። ከጥጥ የተሰሩ ልብሶችን አዩ። አባትዋ ቀይ ቀሚስ፣ ነጭ ሹራብና ቢጫ ካልሲ ገዙላት። ስለዚህ አበባ በጣም ተደሰተች።

2ኛ ቀን

ሞክሼ ፊደላት

ሠ	ሰ

ፊደላቱን ፃፉና አንብቡ።

ሠ ሡ ሢ ሣ ሤ ሥ ሦ

ሰ ሱ ሲ ሳ ሴ ስ ሶ

መነጠል

ነጥላችሁ ፃፉና ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

ምሳሌ:- ሠርግ → ሠ ር ግ

1. ሥጦታ
2. ሰማይ
3. ስቃይ

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎቹን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ::

1. በሱቅ ውስጥ ምን ምን ዓይነት ልብሶች ይሸጣሉ?
2. አበባ ምን ምን ዓይነት ልብሶች ተገዙላት?
3. አበባ የተደሰተችው ለምንድን ነው?

ቃላት

ቃላቱን በብዙ ቁጥር ፃፉ::

ምሳሌ:- ሰው → ሰዎች

1. ልብስ
2. ቀሚስ
3. ሹራብ
4. መቀነት

መፃፍ

በምሳሌው መሰረት ቃላቱን መድቡ::

ኮት	ሸሚዝ	ጉርድ ቀሚስ	የውስጥ ሱሪ
ጋቢ	ኩታ	የአንገት ልብስ	የአበሻ ቀሚስ

	ባህላዊ ልብሶች	ዘመናዊ ልብሶች
ምሳሌ→	ጋቢ	ኮት

3ኛ ቀን

ማዳመጥ

የልብስ ዓይነቶችና ቀለማቸው



ቃላት

በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ።

ምሳሌ፦ ቀይ → የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ቀይ ቀለም አለው።

1. አረንጓዴ 2. ቢጫ 3. ጥቁር 4. ነጭ

ሞክሼ ፊደላት

ጸ	ፀ

ፊደላቱን ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

ጸ ጹ ጺ ጻ ጼ ጽ ጾ ፀ ፁ ፂ ፃ ፄ ፅ ፆ

ማጣመርና መነጠል

አጣምራችሁ ፃፉና አንብቡ።

ጸ - ሀ - ይ ፀ - ሀ - ይ


ነጥላችሁ ፃፉና ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

ጸም ፆም

ግለንባብ

አቅጣጫ ጠቋሚ ቃላት

አቅጣጫ ለማመልከት አቅጣጫ ጠቋሚ ቃላትን እንጠቀማለን። እነሱም ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምሥራቅና ምዕራብ ናቸው። በሌላ መልኩ ደግሞ ቀኝ፣ ግራ፣ ራስጌና ግርጌ የተባሉት ቃሎችም አቅጣጫ ጠቋሚዎች ናቸው።



4ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎቹን በትክክል በጽሁፍ መልሱ።

1. ጓደኞቻችሁ በየት በኩል ተቀምጠዋል?
2. መምህራችሁ ከእናንተ በየት በኩል ይገኛሉ?
3. ጥቁር ሰሌዳው ከእናንተ በየት በኩል ይገኛል?
4. ቢሮው ከክፍላችሁ በየት በኩል ይገኛል?
5. አቅጣጫ ጠቋሚ ቃላት ምን ምን ናቸው?



ቃላት

በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ።

ምሳሌ፦ ሰሜን → ቤቴ ከትምህርትቤቱ በስተሰሜን ይገኛል።

ደቡብ ምስራቅ ምዕራብ



መፃፍ

የጥያቄዎቹን መልሶች በፅሁፍ ግለፁ።

1. ምን ምን ዓይነት ልብሶችን ለብሳችኋል?
2. የልብሶቻችሁን ቀለሞች ፃፉ።

1ኛ ቀን

ማዳመጥ



ቀኑብሽ በገና በዓል

ቃላት

በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ።

ምሳሌ:- ውበት → ውበትን መጠበቅ ቆንጆ ያደርጋል።

1. ኩታ 2. የገና በዓል 3. እሩር 4. የባህል ልብስ

ውስብስብ ፊደላት

ሏ	ሟ

ፊደላቱን በደብተራችሁ ዓፉና አንብቡ።

ሏ ሟ

ማጣመር

አጣምራችሁ በመፃፍ አንብቡ።

ምሳሌ:- ሟ ሟ → ሟሟ

1. ባ ሏ 2. ላ ሟ

የፊደላቱን ቦታ በማቀያየር ቃላት መስርቱ።

ምሳሌ:- በሰለ:- ሰለበ

1. ቀመረ 2. ከመረ 3. በደለ

ግለንባብ

የልብስ ጥቅም

ልብሶች ብዙ ጥቅም አላቸው። ብርድን ይከላከላሉ፤ ውበትና ድምቀትን ይሰጣሉ። ሰዎች እንደየሙያቸው የተለያዩ የደንብ ልብሶችን ይለብሳሉ። ለምሳሌ ተማሪዎች፣ መምህሮች፣ ወታደሮች፣ ሐኪሞች የየራሳቸው የደንብ ልብሶች አሏቸው።



2ኛ ቀን

ውስብስብ ፊደላት

ሷ	ሿ

ፊደላቱን በደብተራችሁ ፃፉና አንብቡ።

ሷ ሿ

ማጣመር

አጣምራችሁ በመፃፍ አንብቡ።

ምሳሌ:- ል ብ ሷ → ልብሷ

1. እ ሷ
2. ሻ ሿ


አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

1. ልብሶች ምን ምን ጥቅሞችን ይሰጣሉ?
2. የደንብ ልብስ የሚለብሱ እነማን ናቸው?

ቃላት

በሳጥኖቹ ውስጥ ተስማሚ ቃላትን ፃፉ።



መፃፍ

ዓረፍተነገር ፃፉ።

ምሳሌ፦ ግርጌ → ጋቢዬን ከአልጋዬ ግርጌ አስቀምጣለሁ።

1. ራስጌ
2. ፊትለፊት
3. በስተጏላ


3ኛ ቀን

ማዳመጥ

ቀኑብሽ በገና በዓል

ቃላት

ቃላቱን ከሥዕላዊ መግለጫዎች ጋር አዛምዱ።

“ሀ”		“ለ”	
ሐ	1. ቀሚስ	ሀ.	
	2. ሹራብ	ለ.	
	3. ጋቢ	ሐ.	
	4. ኮት	መ.	
	5. ሸሚዝ	ሠ.	

ውስብስብ ፊደላት

ቧ	ቷ	ቿ

ፊደላቱን በደብተራችሁ ፃፉና አንብቡ።

ቧ	ቷ	ቿ

ማጣመር

አጣምራችሁ አንብቡ።

1. ሹ ራ ቧ
2. ባ ቷ
3. አ ማ ቿ

ግለንባብ

የሀብታሙ መኝታቤት



ሀብታሙ ሁልጊዜ ከትምህርትቤት ሲመለስ ለመጫወት ይቸኩላል። የደንብ ልብሱንና ቦርሳውን ባገኘበት ቦታ ይጥላል። አንድ ቀን እናቱ ወደመኝታቤቱ ገቡ። መኝታቤቱ ተዝረክርኮ አዩ። በጣም ተናደዱ። ሀብታሙን ጠሩትና "ጥፋትህን አውቀሃል?" ሲሉ ጠየቁት። "አዎ እማዬ! አሁን አስተካክላለሁ" አለ። ወዲያው የደንብ ልብሱን ከአልጋው ራስጌ ባለው ቁምሳጥን ውስጥ አጣጥፎ ከተተ። ቦርሳውን ከፊት ለፊት ባለው መደርደሪያ ላይ አስቀመጠ። ጫማውን ከአልጋው ሥር አኖረ። እናቱ ተመልሰው መጡ። ሳቅ አሉና አቅፈው ሳሙት።

4ኛ ቀን

ውስብስብ ፊደላት

ኗ	ኟ

ፊደላቱን በደብተራችሁ ፃፉና አንብቡ።

ኗ ኟ

መካጠል

ፊደሎቹን ነጥላችሁ ፃፉና አንብቡ።

ምሳሌ፦ ኗሪ → ኗ ሪ

1. ምኗ 2. ጎኗ 3. ሞኟ 4. ቀኟ 5. ትንኟ

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎቹን በምንባቡ መሠረት በፅሁፍ መልሱ::

1. የሀብታሙ እናት የተናደዱት ለምንድን ነው?
2. ሀብታሙ በሠራው ጥፋት ተፀፅቶ ምን አደረገ?



ቃላት

ፊደላቱን መድረሻ በማድረግ ቃላትን መሥርቱ::

ምሳሌ፦ ቷ → ጡቷ፣ ባቷ፣ ላቷ፣ ራቷ፣ ፊቷ

1. ቧ
2. ቿ



መፃፍ

በዓውዳመት (በበዓል) ቀን ምን ምን ዓይነት ልብሶችን ትለብሳላችሁ? በጽሑፍ ግለፁ::

1ኛ ቀን

ማዳመጥ



ተሸላሚው ከድር

ቃላት

በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ።

ምሳሌ፦ ንፁህ → ከድር ንፁህ ልብስ ለብሷል።

1. ማጠብ 2. ማጠፍ 3. ማስቀመጥ

ውስብስብ ፊደላት

ዟ	ጚ

ፊደላቱን ዛራና ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

ዟ	ጚ

ማጣመር

ሀ. ፊደላቱን አጣምራችሁ ቃላት መስርቱ።

አ ዟ ሪ አ ዛ ጚ


ለ. የፊደላቱን ቦታ በማቀያየር ቃላት መስርቱ።

ምሳሌ፦ ቀና → ናቀ

1. ላጠ 2. ላገ 3. ሠራ 4. ላብ 5. ረዳ 6. ገዛ

ግለንባብ

የልብስ ንፅህና



የግል ንፅህናን ለመጠበቅ ልብስን ማጠብ አስፈላጊ ነው።
ልብስ በጠጣር፣ በፈሳሽና በዱቄት ሳሙና ይታጠባል።
ልብስ ከታጠበ በኋላ በፀሃይ ወይም በነፋስ ይደርቃል።
የደረቀውን ልብስ አጣጥፎ ማስቀመጥ ተገቢ ነው።
ደርቀው የታጠፉ ልብሶች በልብስ ቁምሳጥን፣ በሳጥን፣ በሻንጣ፣ ወይም በሌሎች ማስቀመጫዎች ይቀመጣሉ።

2ኛ ቀን

ውስብስብ ፊደላት

ዷ	ጇ

ፊደላቱን ፃፉና ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

ዷ ጇ

ማጣመር

ፊደላቱን አጣምራችሁ ቃላትን መስርቱ።

ድ ዷ ደ ጇ

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ በትክክል መልሱ።

1. ልብሳችሁ ሲቆሽሽ ምን ታደርጋላችሁ?
2. የግል ንፅህናችሁን ባትጠብቁ ምን ጉዳት ይደርስባችኋል?

ቃላት

ቃላቱን ከስዕሎቹ ጋር አዛምዱ።

___ ማስቀመጥ ___ ማድረቅ ___ ማጠብ ___ ማጠፍ

			
1.	2.	3.	4.


መፃፍ

በእረፍት ቀናችሁ ወላጆቻችሁን ምን ዓይነት ሥራዎችን በመሥራት ታግዛላችሁ? በዝርዝር ፃፉ።

3ኛ ቀን

ማዳመጥ


ተሸላሚው ከድር

ቃላት

በምሳሌው መሠረት ሌሎች የድርጊት ቅደምተከተል ማሳያ ቃላትን በሳጥኖች ውስጥ ሙሉ።

ምሳሌ



ውስብስብ ፊደላት

ሯ	ፏ

ፊደላቱን ዓራኑና ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

ሯ ፏ

ማጣመር

ሀ. ፊደላቱን በማጣመር ቃላትን ዓራኑና ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

1. ፏ ፏ ቱ
2. አ ገ ሯ

ለ. የፊደላትን ቦታ በማቀያየር ሌሎች ቃላትን መስርቱ።

ምሳሌ፡- ቃጣ → ጣቃ

1. ማገ
2. ደራ
3. ቀራ
4. ራበ
5. ጠና

ግለንባብ

የዝናሽ ልብስ



ዝናሽ የአዲስ አበባ ከተማ ኗሪና ሠራተኛ ናት። ትዳር የላትም። ልብሷን የምታሳጥበው በልብስ አጣቢዎች ነው። አበበ በዚህ ሙያ ከሚተዳደሩ ሰዎች አንዱ ነው። ዘወትር የዝናሽን ልብስ አጥቦ፣ አድርቆ፣ ተኩሶና አጣጥፎ ያስረክባታል። በዚህም ተግባሩ ሁልጊዜ ታመሰግነዋለች።

4ኛ ቀን

ውስብስብ ፊደላት

ጧ	ፏ

ፊደላቱን ፃፉና ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

ጧ ፏ

ማጣመር

ፊደላቱን በማጣመር ቃላትን ፃፉና ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

1. ጧ ፍ
2. ፏ ሂ

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎቹን በምንባቡ መሰረት በቃላችሁ መልሱ።

1. ዝናሽ የምትኖረው የት ነው?
2. የዝናሽን ልብስ ያጠበው ማን ነው?
3. ዝናሽ ልብሷን የምታሳጥበው ለምን ይመስላችኋል?



ቃላት

በ	መ	ጠ	ረ	ሰ	ወ

እነዚህን ፊደላት በተገቢው ቦታ በመጠቀም ቃላት መስርቱ።

ምሳሌ፦ ቀ በ ረ → ቀበረ ፊ ረ ሰ → ፊረሰ

ቀ - ረ ቀ - ረ ቀ - ረ ቀ - ረ



መፃፍ

በሳምንቱ ቀኖች ውስጥ የሰራችኋቸውን ሥራዎች ፃፉ።

ምሳሌ፦ ሰኞ ወደትምህርት ቤት መጣሁ።

1ኛ ቀን



ማዳመጥ

ትንሹ ሰይድ

ቃላት

በክፍት ቦታዎች ተገቢ ቀናትን ፃፉ።

ምሳሌ፦ አንደኛው ቀን <u>ሰኞ</u> ነው።

ሁለተኛው ቀን _____ ነው።

ሶስተኛው ቀን _____ ነው።

ሰባተኛው ቀን _____ ነው።

ውስብስብ ፊደላት

ቈ	ቀዉ	ቀዊ

ፊደላቱን ፃፉና ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

ቈ ቀዉ ቀዊ

መነጠል

ፊደላቱን ነጥላችሁ ፃፉና እያንዳንዱን ፊደል ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

ምሳሌ፦ ቀዉልፍ → ቀዉ ል ፍ

ቀዉርጥ ቈለፈ

ግለንባብ

ዙሪያ ክብ ጨዋታ



በቀለች፣ ከበደ፣ ሰሚራና አሊ የአንድ ሰፈር ልጆች ናቸው። ዛሬ እለቱ እሁድ ነው። ከነበቀለች ሰፈር ትንሽ ሜዳ አለ። ሜዳው ላይ ክብ ሠርተው ይጫወታሉ። የመሃል ዳኛው አሊ ነው። አሊ "ሰኞ" ሲል ሁሉም ይቆማሉ፤ "ማክሰኞ" ሲል ሁሉም ይቀመጣሉ። "ረቡዕ" ሲል ሁሉም ይተቃቀፋሉ። ከነዚህ ውጭ ሌሎቹ ቀናት ሲጠሩ ይንቀሳቀሳሉ። ጨዋታው ተጀመረ። አሊ "ቅዳሜ" አለ። ከበቀለች በስተቀር ሌሎቹ ተቃቀፉ። በቀለች የጨዋታው አሸናፊ ሆነች።

2ኛ ቀን

ውስብስብ ፊደላት

ቋ	ቌ

ፊደላቱን ዓራና ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

ቋ ቌ

መነጠል

ፊደላቱን ነጥላችሁ ዓራና እያንዳንዱን ፊደል ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

ምሳሌ፦ ቋመጠ → ቋ መ ጠ

ቋንቋ ቋንጣ ቋራ

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

1. የእነበቀለች የጨዋታ ህግ ምንድን ነበር?
2. የጨዋታው የመሃል ዳኛ ማን ነበር?
3. ቅዳሜና እሁድ ምን ዓይነት ጨዋታዎችን ትጫወታላችሁ?

ቃላት

ቃላትን በምሳሌው መሠረት መስርቱ።

ምሳሌ፦ ቆመ ብሎ ይቆማል ካለ፣

1. በላ ብሎ → _____ ይላል።
2. ሮጠ ብሎ → _____ ይላል።
3. ጠለፈ ብሎ → _____ ይላል።
4. አጠበ ብሎ → _____ ይላል።

መፃፍ

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ዓረፍተነገር በማዳመጥ በትክክል ፃፉ።

3ኛ ቀን

ማዳመጥ

ትንሹ ሰይድ



ቃላት

በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. ቅዳሜ
2. እሁድ
3. ቀን
4. ሳምንት

ውስብስብ ፊደላት

ጎ	ጉ	ጊ

ፊደላቱን በደብተራችሁ ዓራና አንብቡ።

ጎ ጉ ጊ

ማጣመርና መነጠል

ሀ. ፊደላትን አጣምራችሁ ቃላት አንብቡ።

ጉ ለ መ ና ጉ ል ቆ

ለ. በነጠላ ቁጥር ዓራ።

ምሳሌ፦ ቀኖች → ቀን

1. ሳምንቶች 2. ሰዓቶች 3. ወሮች 4. እለቶች

ግለንባብ

የሳምንቱ ቀኖች

አንድ ሳምንት ሰባት ቀኖች አሉት። እነሱም ሰኞ፣ ማክሰኞ፣ ረቡዕ፣ ሐሙስ፣ አርብ፣ ቅዳሜና እሁድ ናቸው። ሰኞ የመጀመሪያ ዕለት ሲሆን፣ እሁድ ደግሞ የመጨረሻ ዕለት ነው። ለመንግስት ሠራተኞች ከሰኞ እስከአርብ የሥራ ቀኖች ናቸው።



4ኛ ቀን

ውስብስብ ፊደላት

ኳ	ኌ

ፊደላቱን በደብተራችሁ ፃፉና አንብቡ።

ኳ ኌ

ማጣመር

ፊደላትን አጣምራችሁ ቃላት አንብቡ።

ት ኳ ን በ ኳ ላ

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሰረት በቃላችሁ መልሱ።

1. የሥራ ቀናት የሚባሉት ማን ማን ናቸው?
2. የእረፍት ቀናትስ ማንና ማን ናቸው?
3. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርታችሁን መቼ መቼ ታጠናላችሁ?

ቃላት

ቃላቱን በማቃረን አዛምዱ።

"ሀ"	"ለ"
1. ቀን	ሀ. ሞቃት
2. ቅርብ	ለ. ብዙ
3. ነጠላ	ሐ. ሩቅ
4. ቀዝቃዛ	መ. ሌሊት



መላፍ

በምሳሌው መሠረት ባለፈው ሳምንት የሠራችሁትን ፃፉ::

ምሳሌ፦ ቅዳሜ ልብሴን አጠብኩ::

ሀ. እሁድ ለ. ሰኞ ሐ. ማክሰኞ

1ኛ ቀን

ማዳመጥ

አሰፋና ቤተሰቦቹ



ቃላት

በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ።

ምሳሌ፦ ወር → አንድ ወር ሰላሳ ቀናት አሉት።

1. አፈር 2. እርሻ 3. እርከን

ውስብስብ ፊደላት

ኩ	ኡ	ኩ

ፊደላቱን ዛፉና ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

ኩ	ኡ	ኩ

ማጣመር

ሀ. ፊደላቱን አጣምራችሁ ዛፉና ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

1. ኩ ለ ኩ ለ 2. ኡ ል 3. ኩ ተ ኩ ተ 4. ኡ ር ኡ ም

ለ. ቃላቱንና ፊደላቱን አጣምራችሁ ዛፉና አንብቡ።

ምሳሌ፦ ደፈነ-ች → ደፈነች

1. ፈለገ-ች 2. ጠራ-ች 3. ደረሰ-ች 4. ላከ-ች 5. በለጠ-ች

ግለንባብ

ብልኋ ጉንዳን



በአንድ ወቅት አንዲት ብልህ ጉንዳን ነበረች። ሳታስበው አቶ ምስጥ ዘው ብሎ ወደጉድጓዷ ገባ። ምግብም እንድትሰጠው ጠየቃት። ጉንዳንም "ምን ችግር አለው? እሰጥሃለሁ፤ አሁን ግን መጋቢት ስለሆነ እኔም አንተም ፈላልገን እንበላለን፤ በሰኔና በሐምሌ በበጋው ያጠራቀምኩትን እንጋራለን" አለችና ሰደደችው። ወዲያው ግንቦት እንዳለቀ ጉድጓዷን ደፈነች። ምስጥም መግቢያ አጣ፤ መስከረምም ጠባ።

2ኛ ቀን

ውስብስብ ፊደላት

ኣ	ኤ

ፊደላቱን በደብተራችሁ ፃፉና አንብቡ።

ኣ ኤ

ማጣመር

ፊደላቱን አጣምራችሁ ፃፉና ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

ኣ ስ ኣ ኣ ቱ ታ ን ኣ ድ ን ኣ ን

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

1. ምስጥ ወደጉንዳን ጉድጓድ የመጣው ለምንድን ነው?
2. ብልህነት ይጎዳል ወይስ ይጠቅማል? ለምን?

ቃላት

በክፍት ቦታዎች ተስማሚ ቃላትን እያስገባችሁ ፃፉ።

ምሳሌ$_1$ ብልህ ልጅ። ምሳሌ$_2$ ታታሪ ሰው



መፃፍ

በሳጥኑ ውስጥ ያሉትን ቃላት መርጣችሁ በማጣመር ዓረፍተነገር ፃፉ።

አየለች	ነው	ጉበዝ	ታታሪ	ከድር
ናት	ስመኘው	ፋጡማ	አዋቂ	

ምሳሌ፦ አየለች ጎበዝ ናት።

3ኛ ቀን

ማዳመጥ

አሰፋና ቤተሰቡ

ቃላት

በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. አረም
2. መባቻ
3. ማብቂያ
4. ባለቤት

ውስብስብ ፊደላት

ገ	ጉ	ጉ

ፊደላቱን ፃፉና ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

ጐ	ጒ	ጕ

ማጣመር


ፊደላቱን አጣምራችሁ ፃፉና አንብቡ።

ጐ ረ ም ሳ ጐ ብ ኜ ጒ ር ጥ ጒ ል ት

ግለንባብ

የዓመቱ ወራት

አንድ ዓመት አስራ ሁለት ወራት አሉት። እነሱም፣ መስከረም፣ ጥቅምት፣ ህዳር፣ ታህሳስ፣ ጥር፣ የካቲት፣ መጋቢት፣ ሚያዝያ፣ ግንቦት፣ ሰኔ፣ ሐምሌና ነሐሴ ናቸው። በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ጳጉሜ አስራሶስተኛ ወር ተብላ ትቆጠራለች።



4ኛ ቀን

ውስብስብ ፊደላት

ጓ	ጔ

ፊደላቱን በደብተራችሁ ፃፉና አንብቡ።

ጓ	ጔ



መነጠል

ፊደላቱን ነጥላችሁ ፃፉና አንብቡ

ምሳሌ፦ ጓሮ → ጓ ሮ

ጓል ጓን ጓዝ ጓያ ጓዳ

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎቹን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

1. በአንድ ዓመት ውስጥ ስንት ወራት አሉ?
2. በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር አስራሶስተኛዋ ወር ማን ናት?
3. የዓመቱን ወራት በቅደምተከተል ተናገሩ?



ቃላት

በማቃረን አዛምዱ።

“ሀ”	“ለ”
በጋ	ሀ. ጠቀመ
መጣ	ለ. ከፈተ
ጎዳ	ሐ. ሄደ
ደፈነ	መ. ክረምት
አገኘ	ሠ. አጣ



መፃፍ

በቃላቱ ዓረፍተነገር ፃፉ።

1. ጓጉሜ → ጓጉሜ አስራሶስተኛ ወር ናት።
2. ዘመን
3. በጋ
4. ክረምት

1ኛ ቀን

ማዳመጥ



አደይ

ቃላት

በድርጊት ቅደምተከተል መሠረት ክፍት ቦታዎችን ሙሉ።

ምሳሌ፦ አበባና ጓደኛዋ ተያዩ።

	ድርጊት አመልካች ቃላት።
1. አበባና ጓደኛዋ _____።	• ተሳሳሙ
2. አበባና ጓደኛዋ _____።	• ናፍቆታቸውን ተወጡ
3. አበባና ጓደኛዋ _____።	• ተገናኙ
4. አበባና ጓደኛዋ _____።	• ተቃቀፉ

ማጣመርና መነጠል

1. በምሳሌው መሠረት -ች'ን በመጨመር አጣምራችሁ ፃፉ።

ምሳሌ፦ ሠጠ + ች → ሠጠች

1. ሠራ 2. በላ 3. ሄደ

2. በምሳሌው መሠረት -ች'ን እየነጠላችሁ ፃፉ።

ምሳሌ፦ ሳመች → ሳመ - ች

1. ጠራች 2. ነዳች 3. ጠበቀች 4. አቀፈች



ግለንባብ

ስራ ጠባቂዎች



የነብርሃኑ ሰፈር ወጣቶች ወቅታዊ ሰብሎችን ጠብቀው የሚነግዱ ናቸው፡ ፡ ጊዜው ክረምት ነው። የበቆሎ እሸት ንግዱ ተጧጡፏል ፤ የባቄላና አተር እሸት ገበያም ደርቷል። በዚህም ሁኔታ ወጣቶቹ የክረምትና የፀደይ ወቅቶችን አሳለፉ። በጋው ተተካ፤ እሸቶችም ደረቁ። እነብርሃኑ የሚሸጡት ማግኘት አልቻሉም። ስለዚህ ወጣቶቹ በችግሩ ላይ ተወያዩ። በብድር ገንዘብ አገኙ ፤ በብሎኬት ማምረት ስራም ተሰማሩ።

2ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት በፅሁፍ መልሱ።

1. ስራ ጠባቂዎች እነማን ናቸው?
2. የነብርሃኑ ሰፈር ወጣቶች ምን ችግር ገጠማቸው?
3. የነብርሃኑ ሰፈር ወጣቶች ለችግራቸውስ ምን መፍትሔ አገኙ?
4. ወቅት ጠብቆ መነገድ ምን ጉዳት ያመጣል?



ቃላት

በምሳሌው መሠረት ሥሩ።

ምሳሌ፦ እሸቱ ደርቋል።

1. በቆሎው
2. ንግዱ
3. ዝናቡ
4. ገበያው

መፃፍ

የሥርዓተነጥብን ስያሜ ፃፉ።

	ሥርዓተነጥብ	ስያሜው
ምሳሌ →	:	ሁለት ነጥብ
ሀ.	፣	
ለ.	::	
ሐ.	?	


3ኛ ቀን

ማዳመጥ

አደይ

ቃላት

ሳጥኖቹን በተገቢ ቃላት ሙሉ።



ማጣመር

በምሳሌው መሠረት በክፍት ቦታዎች ቃላት አስገቡ።


ምሳሌ፡- አል-ዘነበ-ም → አልዘነበም

1. አል ___ ም 2. አል ___ ም 3. አል ___ ም

ግለንባብ

የዓመቱ ወቅቶች

አንድ ዓመት አራት ወቅቶች አሉት። እነሱም መኸር (መፀው)፣ በጋ (ሀጋይ)፣ በልግ (ፀደይና) ክረምት በመባል ይታወቃሉ። መስከረም፣ ጥቅምትና ህዳር የመኸር ወቅት ናቸው። የበጋ ወቅት ታህሳስ፣ ጥርና የካቲት ሲሆኑ፣ የበልግ ወቅት ደግሞ መጋቢት፣ ሚያዝያና ግንቦት ናቸው። ሌሎቹ ሰኔ፣ ሐምሌና ነሐሴ የክረምት ወቅት ይባላሉ።



4ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ለጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልስ ስጡ።

1. በአንድ ዓመት ውስጥ ስንት ወቅቶች አሉ? ስማቸውን ተናገሩ።
2. የበጋ ወቅት የምንላቸውን ወሮች ዘርዝሩ።
3. በመኸር(መፀው) ወቅት በአካባቢያችሁ ምን ምን ለውጦችን ታያላችሁ?

ቃላት

ዓረፍተነገር ፃፉ።

ምሳሌ፦ ዝናብ → ዝናብ በክረምት ይዘንባል።

1. ክረምት
2. በልግ
3. መኸር
4. በጋ



መላዱ


በዓላቱ የሚከበሩባቸውን ወሮች ፃፉ።

ምሳሌ፦ የዘመን መለወጫ = መስከረም

ሀ. ፋሲካ ለ. አረፋ ሐ. መውሊድ መ. ጥምቀት

1ኛ ቀን

ማዳመጥ



የዛፍ ጥቅም

ቃላት

በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ።

ምሳሌ፦ ድርቅ → ድርቅ ሰዎችን ይጎዳል።

1. አውሎንፋስ 2. ዛፍ 3. አፈር 4. ወንበር

ማጣመር

የጎደሉትን ፊደላት በማሟላት ቃላት መስርቱ።

ምሳሌ፦ መጽ ሐ ፍ → መጽሐፍ


1. ጉድ_ _ 3. ድር_ _ 2. እው_ _ 4. ግብ_ _ 5. ክረ_ _

ግለንባብ

“ሠርገኛ መጣ....”

ጊዜው ውድቅት ነው። ኃይለኛ ዝናብ ይጥላል።

“በዛብህ! በዛብህ! ኧረ በዛብህ!” ተጣራች ባለቤቱ ማለፊያ።



“ምን ሆንሽ?” አለ በዛብህ።

“ውይ! አንተዬ አይታይህም እንዴ?”

“ምኑ?”

“ቤቱ ውስጥ ጎርፍ ገብቶ!”

“ውይ! ውይ! እንዴት ጉድ ተሰራን! በይ ነይ ተከተዪኝ፤ ‘ሠርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ’ አለ ያገሬ ሰው” አለና ዝናብ እየመታቸው የጎርፍ ማፋሰሻ ቦይ መቆፈር ጀመሩ።

2ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት በፅሁፍ መልሱ።

1. የታሪኩ ባለቤቶች እነማን ናቸው?
2. እነበዛብህ ቤት ጎርፍ የገባው ለምን ይመስላችኋል?
3. “ሠርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ” ከሚለው አነጋገር ምን ትረዳላችሁ?



ቃላት

ባለሁለት ፊደላት ቃላት መሥርቱ።

ምሳሌ፦ ጠላ፣ መታ፣ መጣ



መፃፍ

በምሳሌው መሠረት ፃፉ።

ምሳሌ፦ እርከን ይሠራል ካልን፣


1. መፅሐፍ
2. ገበያ
3. ፅሑፍ
4. ግድብ

3ኛ ቀን



ማዳመጥ

የዛፍ ጥቅም



ማጣመር

ሀ. ወደብዙ ቁጥር ለውጡ።

ምሳሌ፦ ቦይ → ቦዮች

1. ዛፍ　　2. እርከን　　3. ወንዝ　　4. ቁስ

ለ. ፊደላቱን በመምረጥና በማጣመር አስር ቃላት መስርቱ።

አ	በ	ጠ	ረ	
ዘ	መ	ቀ	ወ	ምሳሌ፦ አደረሰ
ጋ	ለ	ደ	ሰ	
ጀ	ከ	ገ	ፈ	

ግለንባብ

ጎርፍ መከላከል

ጎርፍ በተፈጥሮ የሚከሰት አደጋ ነው። በክረምት ወቅት ወንዞች ይሞላሉ፤ ጎርፍም ያስከትላሉ። በሰው ህይወት ላይ ችግር ያደርሳሉ። ንብረትን ያሳጣሉ። ቢሆንም የጎርፍ አደጋን መከላከል ይቻላል። በመጀመሪያ ዘይቤዎችን ማወቅ ተገቢ ነው፤ ለምሳሌ ዛፎችን መትከል፣ ቦዮችን ማዘጋጀት፣ እርከን መስራት ጥቂቶቹ ናቸው።



4ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎቹን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

1. ጎርፍን ለመከላከል ምን ማድረግ ይገባል?
2. ከጎርፍ ውጪ የተፈጥሮ አደጋዎች ምን ምን ይመስሏችኋል?

ቃላት

የችግኝ አተካከል የድርጊት ቅደምተከተሎችን በትክክል ሳፉ።



መፃፍ

የመማሪያ ክፍላችሁን ለማጽዳት ምን ምን ታደርጋላችሁ?
በቡድን ተወያዩና የሚከተሉትን ቃላት በመጠቀም
በቅደምተከተል በፅሁፍ መልሱ።

ሀ. በመጀመሪያ ለ. በመቀጠል ሐ. ከዚያ በኋላ መ. በመጨረሻ

1ኛ ቀን

ማዳመጥ



ብልጡ ቀበሮ

ቃላት

በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ።

ምሳሌ፦ ብልጥ → ቀበሮ ብልጥ እንስሳ ነው።

1. ጉርሻ 2. አይብ 3. ነጋዴ

ማጣመር

በፊደላቱ መነሻነት ባለሶስት ፊደላት ቃላትን ተናገሩ።

ምሳሌ፦ ቀ → ቀበረ፣ ቀደሰ፣ ቀመሰ

1. ደ 2. ከ 3. መ 4. ተ 5. ለ

ግለንባብ

መንገደኛውና ተኩላ



አንድ መንገደኛ ከዛፍ ግንድ ጋር የታሰረ ተኩላ ያገኛል። ተኩላውም "እባክህ ፍታኝ" ይለዋል። መንገደኛውም "ምን ገዶኝ" ብሎ ይፈታዋል። በመቀጠል ተኩላው "እበላሃለሁ" አለው። "በል ጦጢት ትፍረድና ትበላኛለህ" አለው። ከዚያ በኋላ ተያይዘው ወደ ጦጢት ሄዱ። ጦጢትም ሰውዬውን "መጀመሪያ ተኩላን ስታገኘው እንዴት ነበር? በድርጊት አሳየኝ" አለችው። ሰውዬውም አስሮ አሳያት። ጦጢትም "በል! ሰውዬ ዱላ ከእጅህ ተኩላ ከፊትህ" አለችው። ሰውዬውም ተኩላውን በዱላው ቀጥቅጦ ገደለው።

2ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

1. ጦጣዋ በመጀመሪያ ምን ብላ ተናገረች?
2. መንገደኛውስ በመጨረሻ ምን አደረገ?
3. ከዚህ ተረት ምን ተማራችሁ?

ቃላት

በምሳሌው መሠረት ሌሎቹን ሃሳቦች በፅሁፍ አሟሉ።

ምሳሌ፦ <u>ከብት</u> ብሎ <u>ከብት አርቢ</u> ካለ

1. እንጀራ 2. መዝሙር 3. ፀጉር 4. ሸማ 5. ጠላ

መፃፍ

የቃሎችን የቦታ ቅደምተከተል አስተካክላችሁ ዓረፍተነገር ፃፉ።

ምሳሌ፦ ገዝቶ መጣ ቡና ከበደ → ከበደ ቡና ገዝቶ መጣ።

1. ተንኮለኛ እንስሳ ቀበሮ ነው
2. ዳኛ ሆነ ቀበሮ
3. አይቡን ጨረሰው በልቶ ቀበሮ

3ኛ ቀን

ማዳመጥ

ብልጡ ቀበሮ

ቃላት

በነጠላ ቁጥር በቃላችሁ ግለፁ።

ምሳሌ፦ መንገደኞች → መንገደኛ

1. ተኩላዎች 2. ጦጣዎች 3. ቀበሮዎች 4. ውሻዎች

መነጠል

በምሳሌው መሠረት ቃላቱን ነጥላችሁ ፃፉ።

ምሳሌ፦ ተማሪዎች → ተማሪ + ዎች

1. አስተማሪዎች 2. ነጋዴዎች 3. ዘለላዎች 4. ዘማሪዎች

ግለንባብ

የራበው መንገደኛ



ከእለታት አንድ ቀን የራበው መንገደኛ የአተር እሸት ያለበት ማሳ አገኘ። ቁጭ አለና አተሩን ከነልባሱ ሲበላ ቆዬ። ጠገብ ሲል ልባሱን እያነሳ መብላት ጀመረ። በጣም ሲጠግብ ደግሞ ከውስጥ የዘሩን ፍሬ እያወጣ መብላት ያዘ። የማሳው ባለቤት ከዛፍ ሥር ሆኖ ታየው ኖሮ "መንገደኛ እንደመጀመሪያውም እንደመጨረሻውም አትብላ፤ እንደመካከለኛው ብላ" አለችው ይባላል።

4ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎቹን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

1. የራበው መንገደኛ በመጀመሪያ ምን አገኘ?
2. የማሳው ባለቤትስ መንገደኛውን ምን ብላ መከረችው?
3. ከተረቱ ምን ትምህርት አገኛችሁ?



ቃላት

ለጥያቄዎች በፅሁፍ መልስ ስጡ።

ምሳሌ፦ ውሃ ቀዳች ካልን

1. እርሻ 2. ፅሁፍ 3. ጥናት 4. ግንብ 5. እንጨት



መፃፍ

የአተር እሸት ክፍሎችን ዘርዝራችሁ ፃፉ።

1ኛ ቀን

ማዳመጥ



የእንቆቅልሽ ምንነት

ማጣመር

ሀ. ቃላቱን በምሳሌው መሠረት በአሉታ ፃፉ።

ምሳሌ፦ አውቃለሁ → አላውቅም

1. እወዳለሁ 2. እመጣለሁ 3. እስቃለሁ 4. እፅፋለሁ

ለ. አጣምራችሁ ቃላትን በቃላችሁ መሥርቱ።

1. እ ን ቆ ቅ ል ህ 2. ም ን አ ው ቅ ል ሽ

ሐ. አጣምራችሁ ፃፉና ቃላትን መስርቱ።

ምሳሌ፦ አዲስ + አበባ → አዲስ አበባ

1. ንፋስ + ስልክ 2. ሸሮ + ሜዳ 3.አዲስ + ከተማ

ግለንባብ

የትምህርትቤት ጓደኛሞች

እሱባለውና ነፃነት ጓደኛሞች ናቸው። ወደትምህርትቤት ሲሄዱ እንቆቅልሽ መጫወት ይወዳሉ።



እሱባለው፦ “እንቆቅልሽ?”

ነፃነት፦ “ምን አውቅልህ?”

እሱባለው፦ “ስሄድ አገኘኋት ስመለስ አጣኋት?”

ነፃነት፦ “ጤዛ።”

ነፃነት፦ “አባ ሲሏቸው ቆብ የላቸው?”

እሱባለው መልሱ ጠፋው። ነፃነት “ሀገር ስጠኝ” አለችው። “አዲስ አበባን ሰጥቼሻለሁ” አላት። “አዲስ አበባ ተቀምጬ ምን አጥቼ፤ ሁሉ በእጄ ሁሉ በደጄ፤ አባጨጓሬ ነው። በል የእኔን ቦርሳ ተሸክመህ ትምህርትቤት ታደርሳለህ” አለችው።

2ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎቹን በምንባቡ መሰረት በቃላችሁ መልሱ።

1. ከጓደኞቻችሁ ጋር ምን ምን ዓይነት ጨዋታዎችን ትጫወታላችሁ?
2. እሱባለው ነፃነትን ምን ብሎ ጠየቃት?
3. ነፃነትስ ምን ብላ መለሰችለት?
4. እሱባለው የነፃነትን ቦርሳ ከትምህርትቤት ያደርሰዋል? ለምን?

ቃላት

ቃላቱን በአምንታ ፃፉ።

ምሳሌ፦ አልሰጠሁም → <u>ሰጠሁ</u>።

1. አልሠራሁም
2. አልበላሁም
3. አልተኛሁም
4. አልቀረሁም
5. አልጠጣሁም

መፃፍ

ሁለት ሁለት እየሆናችሁ እንቆቅልሽ ፃፉና በክፍል ጓደኞቻችሁ ፊት ተጠያየቁ።

ምሳሌ፦ ሰይድ፦ እንቆቅልሽ?

ሔለን፦ ምን አውቅልህ?

ሰይድ፦ ስሄድ አገኘኋት ስመለስ አጣኋት?

ሔለን፦ ጤዛ።

3ኛ ቀን



ማዳመጥ

የእንቆቅልሽ ምንነት



ቃላት

በምሳሌዎቹ መሠረት ሥሩ።

እኔ	እኛ	አንተ	አንቺ	እናንተ
እሄዳለሁ	እንሄዳለን	ትሄዳለህ	ትሄጃለሽ	ትሄዳላችሁ
እሱ	እሷ	እነሱ		
ይሄዳል	ትሄዳለች	ይሄዳሉ		

ሀ. እመጣለሁ ለ. እሠራለሁ ሐ. እፅፋለሁ



መነጠል

በምሳሌው መሠረት ሥሩ።

ምሳሌ፦ ተጠየቀ → ተ _ ጠየቀ

1. ተጨፈረ
2. ተቆፈረ
3. ተነጠለ
4. ተጨመረ
5. ተነገረ
6. ተመለሰ



ግለንባብ

የእንቆቅልሽ ይዘቶች

የእንቆቅልሽ ጥያቄዎች እንስሳትን፣ ተክሎችንና ምግቦችን በሚመለከት ይቀርባሉ። በተጨማሪም የሰውነት አካላትንና ቁሳቁሶችንም በመጠቀም ጥያቄዎች ይቀርባሉ። ለምሳሌ “ዙሮ ዙሮ መዝጊያው ጭራሮ”፣ “መሰላል ያላት ግን ሰው የማይወጣት”፣ “ሺ ዓይን አለው አጥንት የለው” ተብሎ ቢጠየቅ መልሶቹ በቅደምተከተል “ዓይን”፣ “ማሽላ” እና “እንጀራ” ይሆናሉ።

4ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

በምሳሌው መሠረት በክፍል ውስጥ እንቆቅልሽ ተጠያየቁ።


	ጠያቂ	መላሽ
ምሳሌ፦	1. ፀጉሯን አበጥራ ገበያ የምትወጣ	ግራምጣ ወይም ሱፍ → ከተክል።
	2. አባ ሲሏቸው ቆብ የላቸው	አባጨጓሬ → ከእንስሳት።
	3. አራት እግር ያለው ወንዝ አይሻገር	አልጋ → ከቁሳቁስ።

ቃላት

ቃላትን በማቃረን አዛምዱ።

"ሀ"	"ለ"
1. ቆመ	ሀ. ቀረ
2. አገኘ	ለ. ተቀመጠ
3. ሞተ	ሐ. ዳነ
4. ወጣ	መ. ገባ
5. መጣ	ሠ. አጣ

ክቦቹን አሟሉ።



መፃፍ

ዓረፍተነገር ፃፉ።

ምሳሌ፦ ተቀመጠ → ጀማል ከወንበር ላይ ተቀመጠ።

1. ተሸከመ 2. አጣ 3. አገኘ 4. ዘመረ

1ኛ ቀን

ማዳመጥ



የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬ ዓይነቶችና ጥቅማቸው

ቃላት

ቃላትን በምሳሌው መሠረት መስርቱ።

ምሳሌ፦ ፍሬ ብለን ፍራፍሬ ካልን

1. ሥር 2. ቅጠል 3. ቅመም 4. ጥሬ

ማጣመር

የፊደላቱን ቦታ በመቀያየር ቃላት መሥርቱ።

ምሳሌ፦ ቀሰለ → ሰቀለ፣ ቀለሰ፣ ሰለቀ

1. ለቀበ 2. ሰጠበ 3. ረጠመ 4. ረከመ

ግለንባብ

የልደት ቀኔ



በልደት ቀኔ ትምህርት መኖሩ አናዶኛል። ከትምህርትቤት ስመለስ ቤታችን አሸብርቋል። በጠረጴዛው ላይ ሻማዎች ተደርድረዋል። አንድ ትልቅ ዳቦም አለ። የፍራፍሬ ዓይነቶች፣ ሙዝ፣ ብርቱካን፣ ፓፓዬ፣ ማንጎ፣ ሃብሃብ ህብር ሠርተው ቀርበዋል። ልክ ወደቤት ስገባ ሁሉም ቤተሰቦቼ "መልካም ልደት!" እያሉ አጨበጨቡ። እኔም ሮጬ የምወደውን ብርቱካን አነሳሁ።

2ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

1. የልደት ቀናችሁን አክብራችሁ ታውቃላችሁ? ምን ምን ይዘጋጅላችኋል?
2. ተራኪዋ ወደቤት ስትገባ ቤተሰቦቿ ምን ብለው ተቀበሏት?
3. ተራኪዋ ሮጣ ብርቱካኑን ያነሳችው ለምን ይመስላችኋል?

ቃላት

ዓረፍተነገር ፃፉ።

ምሳሌ፦ ዘር → አርሶአደሩ ዘር ዘራ።

1. ቅጠል
2. ሙዝ
3. ቆስጣ
4. ሰላጣ
5. ቀይስር

መፃፍ

ቃላትን በየምድባቸው ዘርዝሩ።

ተ.ቁ.	ቅጠላቸው የሚበላ	ግንዳቸው የሚበላ	ፍሬያቸው የሚበላ	ሥራቸው የሚበላ
1	የአበሻ ጎመን	ሽንኮራ አገዳ	ብርቱካን	ካሮት

3ኛ ቀን

ማዳመጥ

የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬ ዓይነቶችና ጥቅማቸው

ቃላት

ቃላትን በየምድባቸው ዘርዝሩ።

የምወዳቸው የምግብ ዓይነቶች	የማልወዳቸው የምግብ ዓይነቶች

ማጣመር

ፊደላቱን በማጣመር ድምፅ በማሰማት አንብቡ።


ምሳሌ፦ ት - ላ - ት - ል → ትላትል

1. ሥ - ራ - ሥ - ር
2. ገ - ደ - ላ - ገ - ደ - ል
3. ብ - ረ - ታ - ብ - ረ - ት
4. ጅ - ላ - ጅ - ል

ግለንባብ

እኔ ማን ነኝ?

ክፍራፍሬዎች እመደባለሁ። ቅርፄ ክብ ነው። ስበስል መልኬ ወደቢጫ ያደላል። ተልጬ እበላለሁ። በውስጤ ከስምንት እስከአስር የሚደርሱ ክፍልፋዮች አሉኝ። በየክፍልፋዮቹ ውስጥ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ዘሮች አሉ። ሰዎች ሲመገቡኝ በጣም የምጣፍጥና ጤና የምሰጥ ነኝ። እኔ ማነኝ?



4ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

በምንባቡ መሠረት ጥያቄዎችን በቃላችሁ መልሱ።

1. ብርቱካን ምን ዓይነት ቅርጽ አለው?
2. ብርቱካን ሲበስል ምን ዓይነት መልክ ይኖረዋል?
3. ክብ ቅርጽ ያላቸውን ሌሎች የፍራፍሬ ዓይነቶች ተናገሩ?


ቃላት


በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. ብርቱካን 2. ፓፓያ 3. ሃብሃብ 4. ማንጎ 5. ሙዝ

መፃፍ

ክቦቹን በተገቢ ቃላት አሟሉ።





1ኛ ቀን



ማዳመጥ

ሐናና የምግብ ምርጫዋ

ቃላት

ዓረፍተነገር ፃፉ።

1. መረጠች
2. ተደነቀች
3. መጠነች
4. ተመገበች

ማጣመር


የጎደሉ ፊደላትን በማሟላት ቃላት መሥርቱ።

ምሳሌ፦ ወ _ ወ _ → ወ<u>ረ</u>ወ<u>ረ</u>፣ ወ<u>ሰ</u>ወ<u>ሰ</u>፣ ወ<u>ለ</u>ወ<u>ለ</u>

1. ቀ _ ቀ _
2. መ _ መ _
3. ሰ _ ሰ _
4. ጠ _ ጠ _
5. ፈ _ ፈ _

ግለንባብ

የጓሮ አትክልት ቦታ አዘገጃጀት



የጓሮ አትክልት ቦታን ለማዘጋጀት የሚከተሉትን ተግባራት በቅደምተከተል ማከናወን ያስፈልጋል። በመጀመሪያ የመትከያ ስፍራን መምረጥ ተገቢ ነው። በመቀጠል ቦታውን መመንጠር፣ መቆፈርና ደጋግሞ ማለስለስ ያስፈልጋል። በመጨረሻም መደብ ማዘጋጀትና የውሃ ማፋሰሻ ቦዮችን ማውጣት ይኖርብናል።

2ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ለጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልስ ስጡ።

1. የጓሮ አትክልት ቦታን ለማዘጋጀት ምን ምን ነገሮች ያስፈልጋሉ?
2. የጓሮ አትክልት ተክላችሁ ታውቃላችሁ? ምን ምን?

ቃላት

ዓረፍተነገር ፃፉ።


ምሳሌ፦ አጠበች → ዘይነባ ልብስ አጠበች።

1. መደበች
2. ጀመረች
3. ተከለች
4. አወጣች

መፃፍ

ቃላቱን በመምረጥ ሳጥኖቹን በቅደምተከተል ሙሉ።

መቆፈር	ማለስለስ	መመንጠር	መመደብ	ቦታ መምረጥ




3ኛ ቀን

ማዳመጥ

ሐናና የምግብ ምርጫዋ

ሥዕሎቹን በዓረፍተነገር ግለጹ።

1.	ምሳሌ፦ ዳስ ተሠርቷል።	
2.		
3.		
4.		
5.		

መነጠልና ማጣመር

የፊደላቱን ቦታ በማቀያየር ወይም በመቀነስ ሌሎች ቃላትን መሥርቱ።

ምሳሌ፦ አስተሳሰረ → አሰረ፣ አሳ፣ አሰሳ፣ አረሰ፣ ሳተ፣ አሳተ፣ ተሳሰረ፣ አሳሰረ

1. አስለቀሰ
2. ብርቅርቅታ
3. አቀማጠለ
4. ደብረማርቆስ



ግለንባብ

የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬዎች ለጤንነት





የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬዎች ለጤንነት የሚሰጡት ጥቅም ብዙ ነው። የጓሮ አትክልትን በበቂ ሁኔታ መትከልና መጠቀም የቤተሰብን ጤንነት ለመጠበቅ ይረዳል። እንዲሁም ለሰውነት ጥንካሬን ይሰጣል። የአስተሳሰብ አድማስንም ያሰፋል። ስለዚህ ሰዎች በበሽታ እንዳይጠቁ ዘወትር አትክልትንና ፍራፍሬን መመገብ ይኖርባቸዋል።

4ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ለጥያቄዎቹ በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልስ ስጡ።

1. ከአትክልት ዓይነቶች ውስጥ ሁለቱን ጥቀሱ?
2. ከፍራፍሬ ዓይነቶች ውስጥ ሁለቱን ተናገሩ።
3. ሥራቸው የሚበሉ ተክሎች ምን ምን ናቸው ?



ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ።

ምሳሌ፦ አጠጣ = ሰውዬው ተክሎችን ውሃ አጠጣ።

1. መረጠ
2. አዘጋጀ
3. መነጠረ
4. ጠቀመ



መፃፍ


?	፣	።	ሥርዓተነጥቦቹን በተገቢ ቦታ ፃፉ።

1. ሃሊማ ጎበዝ ተማሪ ናት
2. ከገበያ ሽንኩርት ቃሪያና ብርቱካን ገዛሁ
3. አትክልትና ፍራፍሬ መመገብ የማይፈልግ ማን ነው

1ኛ ቀን

ማዳመጥ

የግል ንጽህና አጠባበቅ



ቃላት


በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. ማበጠር → ጠጉርን ሁልጊዜ ማበጠር አስፈላጊ ነው።
2. መቦረሽ
3. መታጠብ

ማጣመር


ቃላትን በማጣመር ሌሎች ቃላትን መሥርቱ።

ምሳሌ፡- ምክር ቤት



ግለንባብ

ታሞ ከመማቀቅ...



አንድ ቀን የሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች፣ “ኧረ መምህር! ኧረ መምህር! ጓደኛችንን አመመው” እያሉ ጮኹ። መምህራቸውም፣ “ወደተማሪው ዞር ብለው ምንህን አመመህ?” አሉት። “ሆዴን! ሆዴን!” አለ። ወዲያውኑ ወደ ጤና ጣቢያ ይዘውት ሄዱ። ሐኪሙም ከመረመሩት በኋላ በንፅህና ጉድለት መታመሙን አረጋገጡ። ከዚያም፣ “ይኸውልህ ዘወትር እጆችህን መታጠብ፣ ጥፍሮችህን መቁረጥ፣ ልብሶችህን ማጠብ፣ ጥርሶችህን መቦረሽ ወይም መፋቅ፣ ሰውነትህንና ጠጉርህን መታጠብ ይገባሃል” በማለት መከሩት፤ መድሃኒትም ሰጡት።

2ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

1. ተማሪዎች የጮኹት ለምንድን ነው?
2. ተማሪው የታመመው ለምንድን ነው?
3. እናንተ እንደተማሪው እንዳትሆኑ ምን ማድረግ አለባችሁ?

ቃላት


ዓረፍተነገር ሥሩ።

ምሳሌ፦ ጠረን → የላብ ጠረን መጥፎ ሽታ ያመጣል።

1. ምግብ
2. በሽታ
3. መኝታ
4. ህመም

መሳፍ

በስዕሉ ላይ የምታዩዋቸው ልጆች ምን እያደረጉ እንደሆነ በዓረፍተነገር ግለፁ።

ምሳሌ፦ እጁን እየታጠበ ነው።	
1.	
2.	
3.	

3ኛ ቀን

ማዳመጥ

የግል ንጽህና አጠባበቅ

ቃላት

አባባሎችን በምሳሌው መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ምሳሌ፦ ጥርስ → ይቦረሻል ከተባለ

1. ጥፍር 2. ጠጉር 3. ሰውነት 4. ልብስ 5. እጅ

መነጠል

የመጨረሻዎቹን ቅጥያዎች ከቃላቱ ነጥላችሁ ፃፉ።

ምሳሌ፦ አበጠረች → አበጠረ_ች

1. አፀዳች 2. አነጠፈች 3. አለበሰች 4. አመጣች

ግለንባብ

የግል ንፅህና አጠባበቅ



የግል ንፅህናን መጠበቅ የዘወትር ተግባራችን ነው። ሁልጊዜ ፊታችንን፣ እጆቻችንንና ሰውነታችንን መታጠብ፣ ጥርሶቻችንን መቦረሽ ወይም መፋቅ፣ ጥፍሮቻችንን መቁረጥ ያስፈልጋል። ልብሶቻችንንም ማጠብና መተኮስ አለብን። በተጨማሪም መፀዳጃ ቤታችንን በንፅህና መያዝ የዕለት ተዕለት ተግባሮቻችን ሊሆኑ ይገባል።

4ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

በጧት ተነስታችሁ የግል ንጽህናችሁን ለመጠበቅ ምን ምን ታደርጋላችሁ? ግለፁ።

1. መጀመሪያ 2. በመቀጠል 3. ከዚያ በኋላ 4. በመጨረሻ

ቃላት

በክፍት ቦታዎች በምሳሌው መሠረት ተስማሚ ሐረጋትን ሙሉ።



መፃፍ

በምሳሌው መሠረት ቃላቱን መድቡ።

ውኃ	የጥፍር መቁረጫ	ሳሙና	የጥርስ ቡርሽ
ፎጣ	መስታወት	መፀዳጃ ቤት	ማበጠሪያ
መቀስ	ምላጭ	መርፌ	

በጋራ የምንጠቀምባቸው	በጋራ የማንጠቀምባቸው
መፀዳጃ ቤት	የጥፍር መቁረጫ

13ኛ ሣምንት

1ኛ ቀን



ማዳመጥ

ንፅህና ለጤና

ቃላት

ዓርፍተነገር ፃፉ።

ምሳሌ፦ መሃረብ → ከድር አፍንጫውን በመሃረብ አፀዳ።

1. ቁጣ
2. ጉድጓድ
3. ጉንፋን

ማጣመር

ክፍት ቦታዎችን በተስማሚ ፊደላት አሟሉ።

ምሳሌ፦ አፀዳ፣ አረዳ፣ አገዳ

1.	አ	___	ረ	አ	___	ረ	አ	___	ረ
2.	አ	___	ፈ	አ	___	ፈ	አ	___	ፈ
3.	አ	___	መ	አ	___	መ	አ	___	መ
4.	አ	___	በ	አ	___	በ	አ	___	በ

ግለንባብ

“ትምህርትቤታችን ቤታችን ነው”

ቀኑ ዓርብ ነው። እነሰይድ የመማሪያ ክፍላቸውን እየጠረጉ ጓደኞቻቸው ጠሯቸው። ቆሻሻውን ከክፍሉ በር ላይ ጥለውት ሄዱ። ሰኞ ጧት ስም ጠሪ መምህራቸው ሰይድን፣ ማርታንና ከበደን ጠሯቸው። በመቀጠልም “ትምህርትቤታችን እኮ ቤታችን ነው! ቆሻሻን በተዘጋጀለት ቦታ አስቀምጡ” በማለት መከሯቸው።



2ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎቹን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

1. እነሰይድ ያጠፉት ጥፋት ምንድን ነው?
2. እናንተ እነሰይድን ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር?

ቃላት

በምሳሌዎቹ መሠረት ዓረፍተነገር ፃፉ።

ምሳሌ፦ እርሳስ → እርሳሴ ጠፋ።
እርሳሶች → እርሳሶቼ ጠፉ።

1. መርፌ — መርፌዎች
2. ክፍል — ክፍሎች
3. ግቢ — ግቢዎች

መፃፍ

ድርጊቶችን በቅደምተከተል ፃፉ።

1	2
• ቆሻሻን ማቃጠል • ግቢን መጥረግ • ቆሻሻን ጉድጓድ ውስጥ መጨመር	• እጅን በሳሙናና በውሃ መታጠብ • ወደመፀዳጃ ቤት መሄድ • የመፀዳጃ ቤትን ጉድጓድ አፍ መክደን • በመፀዳጃ ቤት ጉድጓድ አፍ ላይ በትክክል መፀዳዳት

ምሳሌ፦ 1. በመጀመሪያ → ግቢን መጥረግ
ከዚያ በኋላ → ቆሻሻን ጉድጓድ ውስጥ መጨመር
በመጨረሻ → ቆሻሻን ማቃጠል

3ኛ ቀን

ማዳመጥ

ንፅህና ለጤና

ቃላት

ስለታም የሆኑና ያልሆኑ ነገሮችን ዘርዝሩ።

ስለታም የሆኑ	ስለታም ያልሆኑ
ምላጭ	ፎጣ

ማጣመር

ተስማሚ ፊደላትን በመምረጥ ቃላትን በቃላችሁ መስርቱ።

ሰ	ደ	ከ	ሀ	
ብ	ል	ር	ያ	ምሳሌ፦ ጥፍር
ገ	ት	ማ	ቀ	
ነ	ጅ	ጥ	ፍ	

ግለንባብ

በጤንነት ለመኖር



በጤንነት ለመኖር ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው። በቅድሚያ የግልን ንፅህና መጠበቅ ያስፈልጋል። ከሌሎች ሰዎች ጋር በጋራ የማንጠቀምባቸው የንፅህና መጠበቂያ መሣሪያዎችን ማወቅ የግድ ነው። እንደምላጭ፣ መርፌና ሌሎች ስለታም ነገሮችን እንዲሁም የጥርስ ቡርሽና ፎጣዎችን በጋራ መጠቀም የለብንም። ምክንያቱም ለኤች አይ ቪ ኤድስና ለሌሎች ተላላፊ በሽታዎች ያጋልጡናል።

4ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

1. ኤች አይቪ ኤድስ ሲባል ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
2. ኤድስ እንዳይዘን ምን ማድረግ ይኖርብናል?
3. ከሌሎች ሰዎች ጋር በጋራ የማንጠቀምባቸውን ዕቃዎች ዘርዝሩ።



ቃላት

ዓረፍተነገር ፃፉ።

ምሳሌ፦ ወጋች → ዓለሚቱ እጇን በመርፌ ወጋች።

1. ቆረጠች
2. ጠረገች
3. ፋቀች



መፃፍ

ሥርዓተነጥቦችን በትክክል በመጠቀም መምህራችሁ የሚነግሯችሁን ዓረፍተነገሮች አዳምጣችሁ ፃፉ።

14ኛ ሣምንት

1ኛ ቀን

ማዳመጥ

የተመጣጠኑ ምግቦችና አስፈላጊነታቸው



ቃላት

በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. ዓሳ
2. አተር
3. ወተት
4. ሎሚ

ማጣመር

ፊደላቱን በክፍት ቦታዎች በመሳፍ ቃላትን መስርቱ።


ጠ	ደ	ወ	ሰ	ጀ	ፈ	ጨ	ል	ሌ	ጅ

ሰለቀ → ሰለቀ	ጀመረ → ጀመረ	ደረሰ → ደረሰ	ጅማት → ጅማት
_ለቀ → ____	_ መረ → ____	_ረሰ → _____	_ ማት → ____
_ለቀ → ____	_ መረ → ____	_ረሰ → _____	_ ማት → ____

ግለንባብ

“ወይ አለማወቅ!”

“ተረኛ፣ ተረኛ!” አለ ነርሱ። ወይዘሮ ታሪኳ፣ “አቤት!” ብለው የሁለት ዓመት ልጃቸውን ይዘው ገቡ። “ምኑን ነው ያመመው?” ዶክተሯ ጠየቁ። “አያዩትም! ፀጉሩ ሳስቷል፤ ሆዱ ተነፍቷል፤ ድዱም ይደማል” አሉ ወይዘሮ ታሪኳ። ዶክተሯም፣ “በጣም ያሳዝናል፤ እንደዚህ ያደረገው የተመጣጠነ ምግብ አለማግኘቱ ነው። አሁንም ወተት፣ እንቁላል፣ ማር፣ አትክልትና ፍራፍሬ ይመግቡት፤ ቶሎ ይሻለዋል፤ ለአሁኑ ግን መድኃኒት አዝለታለሁ” በማለት አስረዷቸው። ወይዘሮ ታሪኳም “ወይ አለማወቅ! ልጄን በምግብ እጥረት ገድዬው ነበር” በማለት አለቀሱ።



2ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

1. የተመጣጠኑ ምግቦችን አለመመገብ ምን ጉዳት ያደርሳል?
2. ዶክተሯ ወይዘሮ ታሪኳን ምን ብለው መከሯቸው?

ቃላት

በምሳሌው መሠረት ቃላትን መድቡ።

ገንቢ ምግቦች	ኃይልና ሙቀት ሰጪ ምግቦች	ከበሽታ ተከላካይ ምግቦች
ወተት	ማር	ሳመን

መፃፍ

የፊደላትን ቦታ በማቀያየር ወይም በመቀነስ ቃላትን መስርቱ::

ምሳሌ፦ አቀረበች → ቀረ፣ ቀረበ፣ ቀረች፣ ቀበረ፣ አቀረበ...


1. ተመጣጠነ 2. አስፈላጊነት 3. አረጋገጠ

3ኛ ቀን

ማዳመጥ

የተመጣጠኑ ምግቦችና አስፈላጊነታቸው

ሥዕሎቹን ከመግለጫዎቻቸው ጋር አዛምዱ::

	"ሀ"		"ለ"		
1.	ሃይልና ሙቀት ሰጭ ምግቦች	ሀ.			
2.	ከበሽታ ተከላካይ ምግቦች	ለ.			
3.	ገንቢ ምግቦች	ሐ.			

ማጣመር

የፊደላቱን ቦታ በማቀያየር ቃላትን መስርቱ::

ምሳሌ፦ ብ ሃ ል ት → ብልሃት

1. ክ ሪ ብ ት 3. ክ ረ ስ ት

2. ድ ቀ ር ት 4. ጥ ረ ም ት 5. ው ቀ ድ ት



ግለንባብ

ጤናማ አመጋገብ



ጤናማ አመጋገብ ማለት ከየምግብ አይነቱ በተመጣጠነ መልኩ የተዘጋጀ ምግብ መመገብ ማለት ነው። የተመጣጠነ ምግብ ገንቢ፣ ሃይልና ሙቀት ሰጪና በሽታ ተከላካይ ናቸው። አንድ ሰው በየቀኑ ከነዚህ የምግብ አይነቶች ሊያገኝ ይገባዋል። በተጨማሪም በስለው የሚበሉ ምግቦችን በደንብ አብስሎ መመገብና በጥሬው የሚበሉትን ደግሞ አጥቦና ንፅህናቸውን ጠብቆ መመገብ ይኖርበታል።

4ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ለጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልስ ስጡ።

1. ጤናማ አመጋገብ ማለት ምን ማለት ነው?
2. በስለው የሚበሉ ምግቦችን በጥሬው ብንመገባቸው ምን እንሆናለን?
3. በጥሬው የሚበሉ ምግቦችን ለመመገብ መጀመሪያ ምን ማድረግ አለብን?



ቃላት

በምሳሌው መሠረት ቃላትን መድቡ።

ሥጋ	ወተት	እንቁላል	ሰላጣ	ማንጎ
ብርቱካን	ድንች	ሙዝ	ዓሳ	ትርንጎ

በስለው የሚበሉ	በጥሬው የሚበሉ
1. ሥጋ	1. ሙዝ



መፃፍ


የጥያቄውን መልስ ፃፉ።

እንቁላል ለመጥበስ ምን ምን ነገሮች ያስፈልጋሉ?

15ኛ ሣምንት

1ኛ ቀን

ማዳመጥ



የንፅህና ጉድለት ጠንቆች

ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. አስም
2. ተስቦ
3. ተቅማጥ
4. ዓይነማዝ

ማጣመር

ፊደላቱን በማጣመር ቃላትን መስርቱ።

ምሳሌ፦ አሰረ

አ	ሰ	ረ
በ	ለ	ጠ
ደ	ለ	በ

1.	4.
2.	5.
3.	6.

ግለንባብ

“በቁማችን ሞተናል!”



“ኡፍ! ኡፍ ውይ! ውይ! ወይኔ! ራሴ!” እያሉ ያቃስታሉ- አቶ ገዛኸኝ። ጎረቤታቸው አቶ ምንተስኖት፣ “ምን ሆነሃል? ያች አስም ተነሳችብህ እንዴ? ይገርማል! በገዛ እጃችን የበሽታ መራቢያ እንሁን?” አቶ ገዛኸኝ ጥርሳቸውን እያፋጩ፣ “እስቲ ተመልከት! በዙሪያችን ያለው የቆሻሻ ክምር! የቆሻሻው ሽታስ አፍንጫችንን በጥሶ ሊጥለው አይደል?” አሉ። አቶ ምንተስኖት “እኛማ በቁማችን ሞተናል እኮ! ነገ የአካባቢውን ማህበረሰብ ሰብስቤ የፅዳት ዘመቻ ሳላውጅ ከቀረሁ ሞቻለሁ” አሉና እጃቸውን አወናጨፉ።

2ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎቹን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

1. አቶ ምንተስኖት “በቁማችን ሞተናል!” ሲሉ ምን ማለታቸው ነው?
2. አቶ ምንተስኖት እጃቸውን ያወናጨፉት ለምንድን ነው?

ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. ተራባ
2. ተሰበሰበ
3. ተነገረ
4. ተቃጠለ
5. ተከላከለ

መፃፍ

በምሳሌው መሠረት ሥሩ።

	የግል ንፅህና	የአካባቢ ንፅህና
ምሳሌ →	▪ ጥፍር መቁረጥ	▪ ግቢን ማፅዳት

3ኛ ቀን

ማዳመጥ

የንፅህና ጉድለት ጠንቆች

ቃላት

ባዳመጣችሁት መሠረት ባዶ ቦታዎቹን በተስማሚ ቃላት አሟሉ።

1. የ _____ በሽታ ከንፅህና ጉድለት ይመጣል።
2. ቤታችንን ካላፀዳን _____ ያፈራል።
3. _____ የተስቦ በሽታ አስተላላፊ ናት።

ማጣመር

“አል_____ም”ን በመጨመር ቃላትን ፃፉ።

ምሳሌ፦ ታጠበ → አልታጠበም

1. ሠራ　　2. ደረቀ　　3. ሸተተ　　4. ቆፈረ

ግለንባብ

በሽታን መከላከል

በንፅህና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎችን መከላከል ይቻላል። ለምሳሌ ፀጉርን፣ ገላንና እጅን በመታጠብ፣ ልብስን በማጠብ የተስቦ በሽታን እንከላከላለን። ቆሻሻን ሰብስቦ በማቃጠልና በመፀዳጃቤት በመጠቀም የተቅማጥ፣ የዓይን ማዝና የጉንፋን በሽታዎችን መከላከል ይቻላል። በክረምት የሚያቁሩ ኩሬዎችን በማድረቅ የወባ ትንኝ እንዳትራባ በማድረግ የወባ በሽታን መቀነስ ይቻላል።



4ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎቹን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

1. ቆሻሻን ሰብስቦ ማቃጠል ለምን ይጠቅማል?
2. የወባ ትንኝ እንዳትራባ ምን ማድረግ ይገባል?
3. በንፅህና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎች ምን ምን ናቸው?



ማጣመር

በምሳሌው መሠረት ሌሎች ቃላትን መስርቱ።

ምሳሌ፦ ሄደ — ሄደች — ሄድን — ሄዳችሁ

1. አጠበ — — — —

2. ታመመ — — — —

3. ዳነ — — — —



መፃፍ

ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. ያዘ　　2. ታመመ　　3. ተጣላ　　4. ፀዳ

16ኛ ሣምንት

1ኛ ቀን



ማዳመጥ

የተዛባ ፍርድ

ቃላት

በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ።

ምሳሌ፦ ጅብ → ጅብ ደመሞቃት እንስሳ ነው።

1. አህያ
2. ነብር
3. አንበሳ

ማጣመር

ፊደላቱንና ቃላቱን አጣምራችሁ አንብቡ።

ምሳሌ፦ የ + ብረት + ድስት → የብረትድስት

1. የ + በጋ + ፀሐይ
2. የ + ዱር + እንስሳ
3. የ + ቤት + እንስሳ
4. የ + ሰውነት + ክፍል
5. የ + ሌሊት + ወፍ

ግለንባብ

የሌሊት ወፎች



የሌሊት ወፎች ከሌሎች ወፎች ይለያሉ። ሌሎች ወፎች እንቁላል በመጣል ይራባሉ። የሌሊት ወፎች ግን መሰላቸውን ይወልዳሉ። በዚህም ምክንያት ከአጥቢ እንስሳት ይመደባሉ። የሌሊት ወፎች እንደሌሎች ወፎች ክንፍ ቢኖራቸውም ቀን በተቦረቦረ ዛፍ፣ ጨለምለም ባለ ቦታ ወይም በዋሻ ውስጥ ያሳልፋሉ። ሲተኙም ክንፋቸውን በማጠፍ ራሳቸውን ይዘቀዝቃሉ። የሌሊት ወፎች የየራሳቸውን ልጆች በድምፃቸው ይለያሉ። ለስልሳ ቀናት ያህልም ሳያቋርጡ ልጆቻቸውን ይመግባሉ። የሌሊት ወፎች በአማካይ ለአምስት ዓመታት በህይወት ይኖራሉ።

2ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎቹን በምንባቡ መሠረት በፅሑፍ መልሱ።

1. የሌሊት ወፍ ልጇን የምትለየው በምንድን ነው?
2. የሌሊት ወፍ ቀን ቀን የት የት ትውላለች?
3. የሌሊት ወፍ በሕይወት የምትኖረው ለምን ያህል ጊዜ ነው?
4. የሌሊት ወፍ ምን ዓይነት እንስሳ ናት?

ቃላት

ለቃሎቹ ተቃራኒያቸውን ስጡ።

ምሳሌ፦ ሌሊት → ቀን

1. ጨኸት
2. ለስላሳ
3. ብርሃን
4. መውቀት
5. ፍርሃት

መፃፍ

ጥያቄዎቹን በፅሁፍ መልሱ።

1. ደመሞቃት ከሚባሉት እንስሳት ውስጥ አራቱን ፃፉ።
2. እፅዋት በል ከሆኑት እንስሳት ውስጥ ሶስቱን ፃፉ።

3ኛ ቀን

ማዳመጥ

የተዛባ ፍርድ

ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ።

ምሳሌ፦ ቀን → የሌሊት ወፍ ቀን ቀን አትበርም።

1. ብረት
2. ፍየል
3. ላት

ማጣመር

ቃላቱን አጣምራችሁ በመፃፍ አንብቡ።


ምሳሌ፦ ቤተ+ ክርስቲያን → ቤተክርስቲያን

1. ቤተ + መንግስት → _____ 2. ቤተ + መዘክር _____

ግለንባብ

“ጥጋብ ይነዳል ወደረሃብ”

በድሮ ጊዜ ውሻና አህያ ከጌታቸው ቤት ጠፉ። ሲሄዱ፣ ሲሄዱ ዋሉ። ለምለም ሳርና ውሃ ያለበት ደረሱ። ውሻ እጥፍጥፍ ብሎ ተኛ። አህያ ከሳሩ እስኪበቃት ነጭታ ከውሃው ስትጠጣ በጣም ጠገበች። ከዚያ በኋላ ውሻን “ልጮህ ነው” አለችው። ውሻም “ተዪ! ጅብ ይመጣብናል” አላት።



“አህያ የውሻውን ምክር ትሰማለች ብላችሁ ታስባላችሁ?”

እምቢ ብላ “ሃ! ሃ!” ብላ ጮኸች። ጅብ ሰማ። ትንሽ ቆይታም ለሁለተኛ ጊዜ ጮኸች። ጅብ ቀረበ። ውሻም “አረ ተዪ! የቅድሙ ማሰሚያ፣ ያሁኑ ማቅረቢያ ነው” አላት። ለሦስተኛ ጊዜ “ሃ! ሃ! ሃ!” ብላ ጮኸች። ውሻም “በይ የአሁኑ መበያ ነው” አላት። ወዲያው ጅብ መጣና ሆዷን ዘረገፈው። ጅብ ቀና ብሎ ሲያይ ውሻው ተጣጥፎ ተኝቷል። “ደግሞ አንተ ምንድነህ?” አለው። “ብልት አውጭ ነኝ” አለ - ውሻ። “በል ና አውጣልኝ!” አለውና ጅብ ተቀመጠ። ውሻም ልቧን ስልቅጥ አደረገ። ጅብም “ልቧን ቶሎ በል!” አለው። “አይ ጌታው፣ ልብማ ቢኖራት መቼ ትበላ ነበር” ብሎ መለሰለት።

4ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎቹን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

1. አህያ እንድትጮህ የገፋፋት ምንድን ነው?
2. ውሻስ እጥፍጥፍ ብሎ የተኛው ለምንድን ነው?
3. “ጥጋብ ይነዳል ወደረሃብ” ማለት ምን ማለት ነው?
4. ከምንባቡ ምን ተረዳችሁ?


ቃላት

የእንስሳቱን ስም ከድምፃቸው ጋር አዛምዱ።

“ሀ”	“ለ”
1. ውሻ	ሀ. ሃ፣ ሃ፣ ሃ...
2. ድመት	ለ. አ.....ዉ.....አ.....ዉ...
3. ጅብ	ሐ. ዉ፣ ዉ፣ ዉ...
4. አህያ	መ. ሚያው፣ ሚያው ....

መሳፍ


ክቦቹን አሟልታችሁ ሳሉ።



17ኛ ሣምንት

1ኛ ቀን

ማዳመጥ



የህይወት ችሎታ


ቃላት

በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. ድምፅ
2. መርዝ
3. ተናዳፊ
4. ተሳቢ

ማጣመር


ቃላቱን በማጣመር ዓረፍቸው።



ምሳሌ፦ ታማኝ + ውሻ → ታማኝ ውሻ።
1. _____ + _____ → _____
2. _____ + _____ → _____
3. _____ + _____ → _____
4. _____ + _____ → _____

ግለንባብ

ተሳቢና ተራማጅ እንስሳት



እንስሳት በእግራቸው የሚራመዱ፣ በውሃ ውስጥ የሚዋኙ፣ በምድር ላይ የሚሳቡና በሰማይ ላይ የሚበሩ ተብለው በአራት ዋና ዋና ምድቦች ሊከፈሉ ይችላሉ። ተራማጅ እንስሳት የሚባሉት ከቦታ ቦታ በእግራቸው

ይንቀሳቀሳሉ። ለምሳሌ እንሽላሊት፣ አዞ፣ እስስት፣ ኤሊና የመሳሰሉት በእግራቸው የሚንቀሳቀሱ ናቸው።

"ተሳቢ እንስሳት ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱት በምናቸው ነው?"

ተሳቢ እንስሳት የሚባሉት ደግሞ ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱት በደረታቸው እየተሳቡ ነው። ዘንዶ፣ እባብ፣ ትላትልና ቀንድአውጣ በደረታቸው እየተሳቡ የሚንቀሳቀሱ ናቸው።

2ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ለጥያቄዎቹ በትዕዛዙ መሠረት በፅሁፍ መልስ ስጡ።

1. ተሳቢ ከሚባሉት እንስሳት መካከል ሁለቱን ፃፉ።
2. እባብ ከቦታ ቦታ እንዴት ይንቀሳቀሳል?
3. ከተሳቢ ወይም ከተራማጅ እንስሳት አንዱን መርጣችሁ ሳሉና ለመምህራችሁ አሳዩ።

ቃላት

በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ።

ምሳሌ፦ ተሳቢ → ተሳቢ እንስሳ እግር የለውም።

1. ተራማጅ 2. መርዛማ 3. ተናካሽ 4. በራሪ

መፃፍ

በምሳሌው መሠረት ሌሎችን ፃፉ።

ምሳሌ፦ በእግሩ → <u>ይሄዳል</u> ካልን

1. በደረቱ 2. በክንፉ

3ኛ ቀን

ማዳመጥ

የህይወት ችሎታ

ቃላት

በምሳሌው መሠረት ሌሎችን አሚሉ::

ምሳሌ፦ አንበሳ በክርኑ ይደቁሳል::

1. አዞ በጥርሱ
2. ጃርት በእሾኋ
3. አጋዘን በቀንዱ

ማጣመር

ፊደላቱን ከቃላቱ ጋር አጣምራችሁ ፃፉና አንብቡ::

ስለ	እንደ	በ	ከ	ለ

ምሳሌ፦ ስለ + መጣ → ስለመጣ

1. _ +እግር
2. _ + ክረምት
3. _ + በጋ
4. _ + አባቱ
5. _ + ጓደኛ

ግለንባብ

ታማኝ ውሻ



አንድ ቀን አቶ ብርሃኑ ውሻውን አስከትሎ ወደ እንጦጦ ጫካ ሄደ:: ጫካውም በተለያዩ እፅዋት የተሞላ ነው:: በጐች ችግኞቹን ሲበሉ ተመለከተ:: ከውሻው ጋር እያባረራቸው ወደ ዛፎቹ መሀል ገባ::

"አቶ ብርሃኑና ውሻው ወደ ዛፎቹ ሲገቡ ምን የሚያጋጥማቸው ይመስላችኋል?"

በድንገት አንድ የነጋበት ጅብ ከአቶ ብርሃኑ ጋር ተፋጠጠ። ውሻውም በጅቡ ላይ ተከመረበት። ጅቡ አቶ ብርሃኑን ትቶ ወደውሻው ዞረ። በዚህ ጊዜ አቶ ብርሃኑ "ድረሱልኝ ፤ ኡ! ኡ! ኡ!" እያለ ጮኸ። የመናፈሻው ዘበኞችም ጩኸት ወደሰሙበት መሳሪያቸውን ይዘው እየሮጡ ሄዱ። ሲደርሱ ጅቡ ግራ ተጋብቶ ሲቅበዘበዝ አገኙት። ዘበኞቹም በያዙት መሳሪያ ተኩሰው ገደሉት።

4ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

በምንባቡ መሠረት ጥያቄዎችን በቃላችሁ መልሱ።

1. አቶ ብርሃኑ ውሻውን አስከትሎ የሄደው ወደየት ነው?
2. ከአቶ ብርሃኑ ጋር የተፋጠጠው ምንድን ነው?
3. ውሻውስ ምን አደረገ?
4. ተረቱ ምን ያስተምራችኋል?

ቃላት

እግር ያላቸውና እግር የሌላቸው እንስሳትን መድባችሁ ፃፉ።

እግር ያላቸው	እግር የሌላቸው
ምሳሌ፦ አዞ	ምሳሌ፦ እባብ

መፃፍ

ዓረፍተነገር ስሩ።

ምሳሌ፦ በእግር → በእግር መጓዝ ጤናማ ያደርጋል።

1. ስለመጣ
2. ለክረምት
3. በበጋ
4. እንደጓደኛው
5. ከአባቱ ጋር

18ኛ ሣምንት

1ኛ ቀን



ማዳመጥ

“ወይ አጋጣሚ!”

ቃላት

በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. መሰብሰብ 2. መቀጥቀጥ 3. ማሰር 4. መርዳት

ማጣመር

ቃላቱን ወደብዙ ቁጥር ለውጡ።

ምሳሌ፦ ወፍ → ወፎች

1. ትል 2. ጠላት 3. እግር 4. ወቅት

ግለንባብ

የዳዊት ድንጋጤ



ባዩሽ የየካ ክፍለ ከተማ ነዋሪ ናት። ዘወትር ከለገዳዲ ከሰል ትገዛለች። እንደተለመደው ከሰሏን ገዝታ ወደቤቷ መጣች። አንዱን ማዳበሪያ ከሰል ማዕድቤት አስቀመጠች። በመቀጠል ዳዊትን “ደክሞኛል፤ እባክህ ቡና አፍላልኝ” አለችው። ዳዊትም፣ “እሺ እማዬ” አለና እሳት ሊያያይዝ የከሰል ማዳበሪያውን ፈታ።

“ዳዊት ምን የሚያጋጥመው ይመስላችኋል?”

“እማዬ! ኧረ እማዬ! የዛሬውስ ከሰል ሙሉውን ጊንጥ ብቻ ነው!” አላት። “ወይኔ ልጄን! ነደፋህ?” ብላ ከተኛችበት ዘላ ተነሳች። “አይ! የሳይንስ መምህራችን ጊንጦች መርዛማና ጎጂ ነፍሳት እንደሆኑ አስተምረውናል” አላት። እሷም፣ “ጐበዝ የኔ ልጅ! ቆይ፣ ከሰሉን በሌላ እቃ እንገልብጥና ተጠንቅቀን እንግደላቸው” አለችው።

2ኛ ቀን


አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በትክክል በቃላችሁ መልሱ።

1. ጊንጥ ምን አይነት ነፍሳት ነች?
2. ባለታሪኮቹ እነማን ናቸው?
3. ቡና ሊያፈላ የነበረው ማን ነው?
4. ባዩሽ የደስማት ለምንድን ነው?
5. ባዩሽ የምትኖረው የት ነው?

ቃላት

ክቦቹን በተገቢ ቃላት አሟሉ።



መፃፍ

ለተሰመረባቸው ቃላት ተመሳሳያቸውን ጻፉ።

1. እባብ በሰውነት ላይ መርዙን <u>ይረጫል</u>።
2. አንዳንድ የዱር እንስሳት ሰውን <u>ይጎዳሉ</u>።
3. እባቡ እንዲሞት ራስ ራሱን <u>ይቀጠቀጣል</u>።
4. ዘንዶ ጠላቱን የሚያጠቃው <u>በመዋጥ</u> ነው።

3ኛ ቀን

ማዳመጥ

“ወይ አጋጣሚ!”

ቃላት

በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. ጨርቅ 2. እንጨት 3. እግር 4. ሃኪም

ማጣመርና መነጠል


የፊደላቱን ቦታ በማቀያየር ወይም በመቀነስ ቃላትን መስርቱ።

ምሳሌ፦ ተቀነጣጠሰ → ቀጣ፣ ጣሰ፣ ቀጠነ፣ ነጠቀ፣ ተሰነጠቀ...

1. ተበጣጠሰ 2. አተረማመሰ 3. ቀረጣጠፈ

ግለንባብ

አደጋ የሚያደርሱ የዱር እንስሳትና ነፍሳት



በተፈጥሯቸው የሚጠቅሙና ጉዳት የሚያደርሱ የዱር እንስሳትና ነፍሳት አሉ። ጉዳት የሚያደርሱ እንስሳትና ነፍሳት ራሳቸውን ከጠላት ለመከላከል የተለያዩ እርምጃዎችን ይወስዳሉ።

“ጉዳት የሚያደርሱ እንስሳትና ነፍሳት ሌሎችን የሚጎዱት በምን በምን ሁኔታ ይመስላችኋል”?

ከሰውነታቸው በሚወጡ መርዛማ ነገሮች ሌሎችን ያጠቃሉ፤ እስከሞትም ያደርሳሉ። ለምሳሌ እባብ ሲናደፍ መርዙን ይተፋል። በዚህም ምክንያት መርዙ በሰውነት ይሰራጭና ይገድላል። ጃርት ጠላት ሲመጣባት በሰውነቷ ላይ ያሉትን እሾሆች በመበተን ጉዳት ታደርሳለች። ዘንዶ ጠላቱን በጅራቱ ጠምጥሞ በመያዝና በማዳከም ይውጣል። ጊንጥና የመሳሰሉት ትናንሽ ነፍሳት ደግሞ ጠላታቸውን በመንደፍ መርዛቸውን ይረጩና ጉዳት ያደርሳሉ። አንበሳ፣ ነብር፣ ጅብና የመሳሰሉት ሌሎችን እንስሳትና ሰዎችን በመንከስና በመብላት እስከሞት ያደርሳሉ።

4ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

በመግለጫው መሠረት የእንስሳቱን ስሞች ፃፉ።

1. እሾሆቿን በመበተን ራሷን ከጠላቷ ትከላከላለች።
2. ጠላቱን በጅራቱ ጠምጥሞ በመያዝ አዳክሞ ይውጣል።
3. በመንደፍና መርዙን በመርጨት ይገድላል።
4. በመንከስ፣ ጉሮሮ በማነቅና በመቧጨር ይገድላል።

ቃላት

በምሳሌው መሠረት ሥሩ።

ምሳሌ፦ <u>ዋጠ</u> ብለን መዋጥ ካልን

1. ገደለ
2. ነከሰ
3. ነደፈ
4. በላ
5. ቆረጠ

መፃፍ

በምሳሌው መሠረት መድቡ።

በመንከስ የሚያጠቁ	በመዋጥ የሚያጠቁ	በመንደፍ የሚያጠቁ
አንበሳ	ዘንዶ	እባብ

19ኛ ሣምንት

1ኛ ቀን

ማዳመጥ

“ሁሉም ሙሉ፤ ሁሉም ዝግጁ!”

ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. ጥራጥሬ 2. ቅመማቅመም 3. ፍራፍሬ 4. ቅጠላቅጠል

መነጠል

መነሻ ፊደሉን ከቃሉ ነጥላችሁ ፃፉ።

ምሳሌ፦ አቀረበ → አ - ቀረበ

1. አጠጣ
2. አበላ
3. አደረሰ
4. አበሰለ
5. አደረቀ

ግለንባብ

“አሳን መብላት በብልሃት”



ዘሃራና ጓደኞቿ ወደ ባህርዳር ከተማ ለጉብኝት ሄዱ። ከተማዋ በአሳ ምርት የታወቀች ናት። በየሆቴሉ የአሳ ምግቦች፦ አሳዱለት፣ አሳጉላሽ፣ አሳኮተሌት፣ አሳጥብስና የመሳሰሉት ተዘጋጅተው ይቀርባሉ። ዘሃራና ጓደኞቿም እንደየፍላጎታቸው ከአሳ ምግቦች መርጠው መመገብ ጀመሩ። አየለች ያዘዘችው አሳጥብስ ነበር። ስትበላ የሆነ ነገር ጉንጯን ጠቅ አደረጋት።

“አየለችን ጉንጯን የወጋት ምን ይመስላችኋል?”

“ወይኔ!” አለች። “ምነው?” አለቻት ዘሃራ። “ጉንጩን ወጋኝ!” “አይ አየለች! ‘አሳን መብላት በብልሃት’ ሲባል አልሰማሽም? በይ አሁንም ቀጫጭን አጥንቶች ስለሚኖሩት ተጠንቅቀሽ ብዪ” ብላ አመጋገቡን አሳየቻት።

2ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎቹን በፅሁፍ መልሱ።

1. “አሳን መብላት በብልሃት” ማለት ምን ማለት ነው?
2. የአየለችን ጉንጭ የወጋው ምንድን ነው?
3. የማታውቁትን ምግብ ከመመገባችሁ በፊት ምን ማድረግ አለባችሁ?

ቃላት

በምሳሌው መሠረት ቃላት መስርቱ።

ምሳሌ፦ ፈፀመ → ተፈፀመ

1. አዘጋጀ 2. ጀመረ 3. ረሳ 4. ሰማ 5. ፈጠረ

መፃፍ

ከፍራፍሬ ዓይነቶች አንዱን ምረጡና እንዴት እንደሚበላ ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

ምሳሌ፦ ብርቱካን ይታጠባል፤ ይላጣል (በቢላዋ ይቆረጣል)፤ ይበላል።


3ኛ ቀን

ማዳመጥ

“ሁሉም ሙሉ፤ ሁሉም ዝግጁ!”

ቃላት

ክቦቹን በተገቢ ቃላት አሟሉ።



ማጣመር


በምሳሌው መሠረት ቃላት መስርቱ።

ምሳሌ፦ ክላ → ተክላ

1. ለቀመ 2. ዘራ 3. አጠበ 4. ጨመረ 5. አጠረ

ግለንባብ

አተር



አተር ከጥራጥሬ እህሎች ይመደባል። በእሸትነቱ ተፈልፍሎ ይበላል። ከደረቀ በኋላ ለምግብነት ይውላል። የደረቀው አተር ለወጥ ሲዘጋጅ በመጀመሪያ አፈሩንና ድንጋዩን፣ ሌሎችንም ቆሻሻዎች ለመለየት ይለቀማል። ከዚያ በኋላ ይታጠብና ይደርቃል፤ በመቀጠል ይቆላል፤ ይከካል።

“አተር ከተከካ በኋላ ምን ይደረጋል?”

የተከካው አተር እንደገና በነፋስ ይዘራል፤ በደንብ ይበጠራል። ከዚህ በኋላ እንደየአቆላሉ ብስለት ክክ ወይም ተፈጭቶ ሽሮ ይሆናል። ሰዎች የሽሮውን ጣዕም ለመጨመር ነጭ ሽንኩርት፣ ዝንጅብል፣ ነጭቅመም፣ በሶብላና የመሳሰሉትን ቅመሞች ከሽሮው ክክ ጋር ቀላቅለው ያስፈጫሉ። ይህም ሽሮወጡን እንዲጣፍጥ ያደርገዋል።

4ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት


ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

1. ከአተር ሽሮ ለማዘጋጀት ምን ምን ማድረግ ያስፈልጋል?

   በመጀመሪያ _____፣_____፣ _____፣ _____ በመጨረሻ _____

ቃላት

በምሳሌው መሠረት ክቦችን አሟሉ።



መፃፍ

በምሳሌው መሠረት አሟልታችሁ ፃፉ።

ምሳሌ፡ አተር በሰፌድ ይነፈሳል።

1. አተር በወፍጮ
2. አተር በብረት ምጣድ
3. አተር በውሃ
4. የአተር ክክ በነፋስ
5. የአተር እሸት በእጅ

20ኛ ሣምንት

1ኛ ቀን

ማዳመጥ



የምግብ ዝግጅት ባለሙያ

ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ

ምሳሌ፦ ብረትድስት → ብረትድስት ወጥ ለመስራት ያገለግላል።

1. መጥበሻ 2. ማማሰያ 3. ማንኪያ 4. ቢላዋ

ማጣመር

ፊደላቱን አጣምራችሁ ቃላት መስርቱ።

ምሳሌ፦ ዘ-ጋ → ዘጋ

1. ቆ - ረ - ሰ
2. ቀ - ነ - ሰ

ምሳሌ፦ ዘ - ጋ - ጋ → ዘጋጋ

1. ቆ - ራ - ረ - ሰ
2. ቀ - ና - ነ - ሰ

ግለንባብ

ጤናዬና ቤተሰቦቿ

ጤናዬና ባለቤቷ የመንግስት ሠራተኞች ናቸው። በትዳር ዘመናቸው ሁለት ልጆች ወልደዋል። በእነጤናዬ ቤተሰብ ለወንድና ለሴት ተብሎ የተለየ የሥራ ክፍፍል የለም። እለቱ ቅዳሜ ነበር። ጤናዬ ወደገበያ ስትሄድ ባለቤቷ አቶ ጥግነህ ደግሞ እንጀራ ለመጋገር በዝግጅት ላይ ነበር።



ሊጡን እንዳሰፋ የግቢው በር ተንኳኳ። በሩን ለመክፈት እየሮጠ ሄደ። “ውይ! ጤናዬ አንቺ ነሽ እንዴ?” ብሎ የያዘችውን ዕቃ ተቀበላት። ተያይዘው ወደቤት ገቡ። በዚህ መሃል ያሰፋው ሊጥ ትዝ አለው። “ውይ! ውይ!” እያለ ወደ ማዕድቤት ሮጠ።

“አቶ ጥግነህ ምን የሚያጋጥመው ይመስላችኋል?”

ቶሎ ብሎ አክንባሎውን ከፈተ። እንጀራው አርሯል፤ ደነገጠ። ዞር አለና መሰቅሰቂያ አነሳ። የእንጀራውን ጠርዝ በመሰቅሰቂያው ሰቀሰቀው ፤ ቢቆራረስም እንደምንም ለቀቀለት። ከዚያ በኋላ እሳቱን ቀነሰውና በተደጋጋሚ ምጣዱን በጎመን ዘር አሰሰው። ሊጥም አሰፋበት፤ ትንሽ ቆይቶ ከፈተው። ያልተቆረሰ እንጀራ አወጣ። ሳቅ አለ።

2ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሰረት መልሱ።

1. አቶ ጥግነህ እንጀራው ያረረበት ለምንድን ነው?
2. አቶ ጥግነህ እንጀራው ሲያርበት ምን አደረገ?
3. ከእነጤናዬ ቤተሰብ ምን እንማራለን?

ቃላት

በምሳሌው መሠረት ጻፉ።

ምሳሌ፦ እንጀራ → ይጋገራል።

1. ወጥ 2. ጥብስ 3. ዳቦ 4. ጠላ 5. ጠጅ

መፃፍ

ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. ሰቀሰቀ 2. አሰሰ 3. ቆረሰ 4. አረረ

3ኛ ቀን

ማዳመጥ

የምግብ ዝግጅት ባለሙያ

ቃላት

የሚከተሉት ቁሶች ለምን አገልግሎት እንደሚውሉ ለመምህራችሁ ግለፁ።

1. ምጣድ 2. አክንባሎ 3. መሰቅሰቂያ 4. ማማሰያ

ማጣመር

ቃላቱን ወደብዙ ቁጥር ለውጡ።

ምሳሌ፦ ብርጭቆ → ብርጭቆዎች

1. ኩባያ 2. ስኒ 3. ሹካ 4. ማንኪያ

ግለንባብ

የምግብና የመጠጥ ቁሶች



የምግብና የመጠጥ ቁሶች እንደየአገልግሎታቸው ይለያያሉ። ለምሳሌ ዝርግ ሳህን፣ መሶብና ትሪ ለእንጀራና ለዳቦ ማቅረቢያ ያገለግላሉ።

"ጎድጓዳ ሳህንና ዘመናዊ ሽክላድስት ለምን ለምን ይጠቅማሉ?"

ጎድጓዳ ሳህንና ዘመናዊ የሸክላ ድስት ለሥጋ፣ ለአትክልት፣ ለዶሮ ወጥ ማቅረቢያ ያገለግላሉ። ሹካና ማንኪያ ደግሞ ለፓስታና ለመኮረኒ እንዲሁም ለአትክልት መመገቢያ ይጠቅማሉ። ለመጠጥ ማቅረቢያ ደግሞ ስኒዎችን፣ ብርጭቆዎችንና ኩባያዎችን መጠቀም እንችላለን። የሻይ ስኒዎች ሻይ ለመጠጫ፣ የቡና ስኒዎች ቡና ለመጠጫ ያገለግላሉ። ብርጭቆዎች ለስላሳና ውሃ የመሳሰሉት ይጠጣባቸዋል። ኩባያዎች ደግሞ ለወተት፣ ለአጥሚትና ለሾርባ መጠጪያነት ያገለግላሉ።

4ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሰረት በጽሑፍ መልሱ።

1. በስዕሉ ላይ ያሉ እቃዎችን ዘርዝራችሁ ፃፉ።
2. ፓስታና መኮረኒ ለመብላት ምን ምን ዕቃዎች ያስፈልጋሉ?
3. ቡና በምን ይጠጣል?
4. ውሃ በምን ይጠጣል?
5. እንጀራ በምን ይቀርባል?

ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. ጠበሰ
2. ቀቀለ
3. ጨለፈ
4. ከተፈ

መፃፍ

የቃላቱን ቦታ በማስተካከል ዓረፍተነገር ሥሩ።

ምሳሌ፦ ጧት፣ በላሁ፣ መኮረኒ → መኮረኒ ጧት በላሁ።

1. ዶሮወጥ፣ ቀረበልኝ፣ ለምሳ → _____
2. ሻይ፣ ጠጣሁ፣ በሻይ ስኒ → _____
3. እንጀራ፣ በላሁ፣ በትሪ → _____

21ኛ ሣምንት

1ኛ ቀን

ማዳመጥ



“ታላላቆቻችሁን አክብሩ”

ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ።

ምሳሌ፦ ራበው → ጀማል ራበው።

1. አዘኑ 2. ተሸከሙ 3. አሳየች 4. ረዳ

ማጣመር

ቃላቱን በምሳሌው መሠረት በአሉታ ፃፉ።

ምሳሌ፦ ሰጠ → አልሰጠም።

1. ተቀበለ 3. ታመመ 2. ታዘዘ 4. ያዘ

ግለንባብ

መስጠትና መቀበል

አሸናፊ፣ ዘመናይና ዘቢባ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። አንድ ቀን ለእረፍት እንደወጡ፣ ዘቢባ “ዶሮ እንቁላል ይጥላል?” ብላ ጠየቀቻቸው።



“ዘቢባ ጥያቄውን ስታቀርብ አሸናፊ ምን የሚል ይመስላችኋል?”

አሸናፊም “አሁን ይሄ ጥያቄ ነው?” ብሎ ሳቀባት። ዘመናይም “አንተ ደግሞ ሁልጊዜ ራስህን ከፍ አድርገህ ታያለህ!” አለችው። አሸናፊም “አይ! ማየት ሳይሆን እንቁላል የማይጥል ዶሮ ያለ ይመስል፣ ገርሞኝ እኮ ነው” አለ። ዘመናይም “ይኸውልህ መልሱ ዶሮ እንቁላል ሊጥልም ላይጥልም ይችላል ነው። ምክንያቱም ሴትዶሮ እንጂ ወንድዶሮ እንቁላል አይጥልም” አለችው። ዘቢባም “ተመልከት ሁልጊዜ አውቃለሁ አትበል። እውቀትህን ለሌሎች መስጠት ብቻ ሳይሆን መቀበልንም ተማር” በማለት ዘመናይን አቅፋ ሳመቻት።

2ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ለጥያቄዎቹ በጽሑፍ መልስ ስጡ።

1. መስጠትና መቀበል ሲባል ምን ይመስላችኋል?
2. ዘመናይ አሸናፊን የተቆጣችው ለምንድን ነው?
3. ዘቢባ ዘመናይን አቅፋ የሳመቻት ለምንድን ነው?

ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ።

ምሳሌ፦ ሸኘ → ጀማል አዛውንቱን ሸኘ።

1. ተቀበለ 2. ሮጠ 3. ተሸከመ 4. መለሰ

መፃፍ

ለጥያቄው በጽሑፍ መልስ ስጡ።

1. እናንተ በእድሜ የገፉ አዛውንት ቢገጥሟችሁ በምን በምን ታግዟቸዋላችሁ? በዝርዝር ፃፉ።

3ኛ ቀን



ማዳመጥ

ታላላቆቻችሁን አክብሩ



መነጠል

የመጀመሪያውን ፊደል ነጥላችሁ ፃፉ።

ምሳሌ፦ ተሰጠ → ተ - ሰጠ

1. ተወደደ 2. ተቀጣ 3. ተከመረ 4. ተሰደበ



ግለንባብ

የመልካም ስነምግባር መገለጫዎች

ሀቀኝነት፣ ሰዎችን ማክበርና ታማኝነት የመልካም ሥነምግባር መገለጫዎች ናቸው። ሀቀኝነት ሲባል እውነትን መናገር፣ በእውነት መስራት፣ አለመዋሸት ማለት ነው።

"ታማኝነት ማለት ምን ማለት ነው?"

ታማኝነት ደግሞ የተሰጠን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት፣ አደራን ተቀብሎ በአግባቡ መያዝ፣ የሰውን ንብረት ካልተፈቀደ በስተቀር አለመንካት፣ አለመስረቅና የመሳሰሉትን ድርጊቶች አለመፈፀም ናቸው። ሰዎችን ማክበር ሲባል ደግሞ አለመሳደብ፣ ለትልልቆች ቅድሚያ መስጠት፣ መታዘዝ፣ ጓደኛን መውደድ፣ ከራስ ይልቅ ለሰዎች ማሰብን ያጠቃልላል።

4ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

በምሳሌው መሠረት ቃላቱን መድቡ።

መስረቅ	እውነት መናገር	መዋሸት
ለራስ ቅድሚያ መስጠት	አለመታዘዝ	ታማኝነት
መምከር	ሰውን ማክበር	መሳደብ
ሀቀኝነት		

	ጥሩ ስነምግባር	ጥሩ ያልሆነ ስነምግባር
ምሳሌ፡-	እውነት መናገር	መስረቅ

ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. ሸለመ
2. ወደደ
3. ነካ
4. መከረ
5. ዋሸ
6. ሠረቀ

መፃፍ

የቃላቱን ቅደምተከተል በማስተካከል ዓረፍተነገሩን አስተካክላችሁ ፃፉ።

1. መምህራንን እወዳቸዋለሁ በጣም
2. አዛውንቱን ረዳኋቸው በሥራ
3. ርዕሰ መምህራችን ሰበሰቡን ዛሬ
4. ተሸከመ እቃ አባባ
5. አባባን አገዝኳቸው ሮጬ

1ኛ ቀን

ማዳመጥ



ሃላፊነትን መቀበል

ቃላት

በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. የሥራ ድርሻ 2. ማገዝ 3. ሃላፊነት 4. መቀበል

ማጣመር

ሀ. ቃላቱን አጣምራችሁ ፃፉ

ምሳሌ፦ ሥነ + ምግባር → ሥነምግባር


1. ሥነ + ህይወት 2. ሥነ + ጥበብ 3. ሥነ + ፍጥረት

ለ. ፊደላቱን አጣምራችሁ ቃላቱን ተናገሩ።

1. ሰ - ን - ደ - ቅ - ዓ - ላ - ማ 2. መ - ከ - ባ - በ - ር

ግለንባብ

የግርማ ጥፋት



“እማዬ! ኧረ እማዬ!” ሰብለ ተጣራች። “አርፋችሁ አትበሉም? ምን ያስለፈልፍሻል?” አሏት እናታቸው። “ይሄ ግርማ፣ የራሱን ምግብ ጨርሶ የእኔን ይበላል” እያለች አለቀሰች። “ኧረ እማ! አውቃ ነው፤ ውሸቷን ነው። የራሴን ምግብ እየበላሁ ነው” አላቸው። እናታቸውም ከጓዳ እየሮጡ መጡ። የግርማ ምግብ አልቋል።

የሰብለ ደግሞ ተደፋፍታል። “ምነው! ምነው! ግርማ?” አሉት። “እማዬ ስላልጠገብኩ ነው” አለ። “ካልጠገብክ ጨምሩልኝ አትልም?” ግርማም፣ “እማ፣ ሁለተኛ አይለምደኝም፤ ለዛሬ ይቅር በይኝ” አላቸው። እናታቸውም፣ “አዎ፣ መዋሸትና የሰውን ገንዘብ መቀማት ጥሩ ያልሆነ ስነምግባር ነው” በማለት መከሩት።

2ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት በፅሁፍ መልሱ።

1. ሰብለና ግርማ የተጣሉት በምን ምክንያት ነው?
2. ጥፋት ያጠፋው ማን ነው?
3. እናቱ ግርማን ምን ብለው መከሩት?

ቃላት

በተገቢ ቃላት ሠንጠረዡን አሟሉ።

ህግ እናት ማክበር	1. ህግ ማክበር 2. እናት ማክበር 3. _____ 4. _____ 5. _____

መፃፍ

ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. ንብረት 2. ሥነሥርዓት 3. ሥነምግባር 4. ማክበር

3ኛ ቀን

ማዳመጥ

ሃላፊነትን መቀበል

ቃላት

ቃላትን በማቃረን አዛምዳችሁ ፃፉ

“ሀ”	“ለ”
1. መብላት	ሀ. መዘግየት
2. መፍጠን	ለ. መጀመር
3. መጥፎነት	ሐ. ጥሩነት
4. መጨረስ	መ መጠጣት

ማጣመር

ሀ. የተጓደሉ ፊደላትን በመሞከር ቃላት መስርቱ።

1. አከ _ _ 2. ተንከባ _ _ 3. ሥነምግ _ _ 4. መም _ _

ለ. ቃሉን ከቅጥያው ጋር (-ነት) በማጣመር ሌላ ቃል መስርቱ።

ምሳሌ፦ ክፉ + ነት → ክፉነት

ሀ. ታማኝ ለ. ደግ ሐ. ቅን መ. የዋህ ሠ. ብልህ

ግለንባብ

የጊዜ አጠቃቀም



ማንኛውም ሰው ጊዜውን በአግባቡ መጠቀም ይኖርበታል። በዚህም መሠረት ተማሪዎች የትምህርት ቀናትንና የበዓል ቀናትን በመለየት ጊዜያቸውን ከፋፍለው ይጠቀማሉ። ተማሪዎች በየሣምንቱ የዕረፍት ቀን ጊዜያቸውን ከፋፍለው ለመጠቀም ዕቅድ ቢያወጡ ጥሩ ነው። ለምሳሌ ቅዳሜ እስከጧቱ 2:00 ድረስ ልብሳቸውን ለባብሰው ቁርሳቸውን ይበላሉ።

✶✶✶ተማሪዎች ቁርሳቸውን ከበሉ በኋላ ምን ያደርጋሉ ብላችሁ ታስባላችሁ?”✶✶✶

ከ2:00 እስከ6:00 የማጠናከሪያ ትምህርት ይማራሉ። ከ6:30 እስከ 7:30 ምሳቸውን ይበላሉ። ከ7:30 እስከ9:00 ያርፋሉ፤ ከ9:00 እስከ 10:00 ይጫወታሉ፤ ከ10:00 እስከ12:00 ወላጆቻቸውን በሥራ ያግዛሉ፤ ከምሽቱ 12:00 እስከ2:00 የቤት ሥራቸውን ይሠራሉ፤ ያጠናሉ። በዚህ መሠረት ያወጡትን ዕቅድ በተገቢ መንገድ የሚጠቀሙ ተማሪዎች መልካም ሥነምግባርን ያዳብራሉ፤ ውጤታቸውም ከፍተኛ ይሆናል።

4ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ለጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልስ ስጡ።

1. ተማሪዎች ምሳቸውን የሚበሉት ከስንት እስከስንት ሰዓት ነው?
2. ወላጆቻቸውንስ የሚረዱት ከስንት እስከስንት ሰዓት ነው?
3. የሚጫወቱትስ ከስንት እስከስንት ሰዓት ነው?

ቃላት

ለጥያቄው ተገቢ ምላሽ በቃላችሁ ስጡ።

በቀን ውስጥ ስንት የምግብ ጊዜያት አሏችሁ? ስማቸውን ግለፁ።

መፃፍ

የሰኞ የሥራ እቅዳችሁን በተሰጠው ጊዜ መሠረት ፃፉ።

የሰኞ ተግባራት	የተሰጠ ጊዜ
ፊቴን ታጥቤ ቁርሴን እበላለሁ።	ከ1:00 - 1:30
ወደትምህርት ቤት እሄዳለሁ።	
እማራለሁ።	
ወላጆቼን እረዳለሁ።	
አጠናለሁ።	

23ኛ ሣምንት

1ኛ ቀን

ማዳመጥ

የሥርዓተፆታ እኩልነት



ቃላት

ቃላቱን በማንበብ ትርጉማቸውን ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩባቸው።

1. የሥርዓተፆታ እኩልነት
2. እኩል ተሳትፎ
3. ፍትሀዊነት
4. እኩል የሥራ ክፍፍል

ማጣመር

ቃሉን ከቅጥያው ጋር አጣምራችሁ ፃፉ።

ምሳሌ፦ እኩል - ነት → እኩልነት

1. ወንድ - ነት 2. ሴት - ነት 3. ሰው - ነት 4. ልጅ - ነት

ግለንባብ

“ወገን ለወገን”

ነጃትና ደረሰ በዓይንማዝ በሽታ ምክንያት ዓይነስውር ሆነዋል። ሁለቱም የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። ግብረሠናይ ድርጅት እየረዳቸው በአንድ ግቢ ውስጥ ይኖራሉ። በትምህርት ቤታቸውና በቤታቸው መካከል የመኪና መንገድ አለ። ደረሰና ነጃት ወደትምህርትቤታቸው



ለመሄድ መኪና መንገዱን ማቋረጥ አለባቸው። በዚህም የተነሳ የክፍላቸው ተማሪዎች ተወያዩ፤ የሥራ ክፍፍልም አደረጉ። ሁሉም ተማሪዎች በየተራ እነነጃትን ይዘው ወደትምህርትቤት ይመጣሉ፤ ወደቤታቸውም ይመለሳሉ። ስለዚህ ደረሰና ነጃት ያለምንም ስጋት ትምህርታቸውን መከታተል ቻሉ።

2ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት መልሱ።

1. የክፍላቸው ተማሪዎች እነነጃትን ለመርዳት ምን አደረጉ?
2. እናንተስ እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ቢያጋጥማችሁ ምን ታደርጋላችሁ?

ቃላት


ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. እኩል	2. ፆታ	3. ፍትህ	4. የሥራ ድርሻ

መፃፍ

ተስማሚ ቃላትን በሳጥኖች ውስጥ ፃፉ።

የዕድሜ	የሥራ	የባህል	የሀይማኖት	የቋንቋ	የፆታ



3ኛ ቀን

ማዳመጥ



የሥርዓተፆታ እኩልነት

ቃላት

ቃላቱን በማቃረን አዛምዱ።

	“ሀ”		“ለ”
ለ	1. እኩልነት	ሀ.	መናቅ
	2. የበላይነት	ለ.	አድሏዊነት
	3. ማክበር	ሐ.	አንድነት
	4. ልዩነት	መ.	መጉዳት
	5. መጥቀም	ሠ.	የበታችነት


መነጠል

በነጠላ ቁጥር ፃፉ። ምሳሌ፦ ክበቦች → ክበብ

1. ድርጅቶች
2. አድሎዎች
3. ተጎጂዎች
4. ተጠቃሚዎች
5. ስጋቶች

ግለንባብ

የፍትህ ምንነት



ፍትህ ማለት አለማዳላት ማለት ነው። እውነትን መናገር ነው፤ እውነትን መሰረት አድርጎ መሥራት ነው። ፍትህ በትምህርትቤት፣ በቀበሌና በቤተሰባዊ ኑሮ ውስጥ አስፈላጊ ነው። ፍትህ የሰዎች ህይወትና ኑሮ ጥሩ እንዲሆን ያደርጋል። በሰዎች መካከል ምንም አይነት ልዩነትና አድሎ እንዳይፈጠር ይጠቅማል። በጓደኝነትም ደረጃ አንዱ የበላይ ሌላው የበታች እንዳይሆን ያግዛል። ስለዚህ ፍትህ አንዱ ተጎጂ ሌላው ተጠቃሚ እንዳይሆን በማድረግ የሰዎችን መብት ያስከብራል።

4ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት መልሱ።

1. እውነት መናገር ለምን ይጠቅማል?
2. ፍትህ የት የት ይከበራል?
3. ፍትህ ባይኖር ሰዎች ምን ምን ጉዳት ይደርስባቸዋል?

ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. ተጠቃሚ
2. ተጎጂ
3. ተናጋሪ
4. ተቆርቋሪ

መፃፍ


በምሳሌው መሠረት ቃላትንና ሐረጋትን መድቡ።

ማዳላት	መዋሸት
እውነት መናገር	ራስን ብቻ መጥቀም
ትክክለኛ ፍርድ መስጠት	ጓደኛን ማበላለጥ
ሁሉንም ሰው እኩል ማየት	

	ፍትሃዊ የሆነ	ፍትሃዊ ያልሆነ
ምሳሌ፦	እውነት መናገር	ጓደኛን ማበላለጥ

24ኛ ሣምንት

1ኛ ቀን



ማዳመጥ

የአካል ጉዳተኝነት

ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. ጉዳት
2. ድጋፍ
3. ሚና
4. ህብረተሰብ

ማጣመር


በብዙ ቁጥር ፃፉ።

ምሳሌ፦ ተማሪ → ተማሪዎች

1. ጥያቄ
2. ሥራ
3. ዜጋ
4. ሁኔታ

ግለንባብ

ጎበዟ ቆንጂት



ቆንጂት ዓይነስውር ናት። የምትማረው ማየት ከሚችሉ ተማሪዎች ጋር ነው። አንድ ቀን መምህራቸው፣ “ተማሪዎች፣ ገፅ ስምንትን አውጡ” አሉ። በመቀጠል “እስኪ የመጀመሪያውን ጥያቄ መልሱ” በማለት ተናገሩ። ተማሪዎችም “እኔ፣ እኔ” እያሉ እጃቸውን አወጡ። ቆንጂትም እጇን አወጣች። ወዲያውኑ “መምህር ጥያቄው ከመመለሱ በፊት ጥያቄ አለኝ” አለቻቸው። መምህሩም በመገረም “ጥያቄው አልገባሽም እንዴ?” አሏት። ቆንጂትም “ጥያቄውን ለእኔ አላነበቡልኝም፤ ስለዚህ መሳተፍ አልችልም” አለቻቸው። መምህሩ ደነገጡ። “ይቅርታ! ያነበብኩልሽ መስሎኝ ነው።

ሁላችሁም አዳምጡኝ” በማለት ጥያቄውን ተረጋግተው አነበቡላቸው። ከዚያም በኋላ ቆንጂት እንድትመልስ እድል ሰጧት። በሚገባ አብራርታ መለሰች። መምህሩም “ቆንጂት በጣም አመሰግናለሁ! ችሎታሽን ስላሳየሽን እናጨበጭብልሻለን” አሉ። ቆንጂትም “አሁን ምቹ ሁኔታን ፈጥረውልኛል” ብላ ፈገግ አለች።

2ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት በፅሁፍ መልሱ።

1. ቆንጂት ምን ዓይነት ተማሪ ናት?
2. ቆንጂት መምህሯን ምን ብላ ጠየቀቻቸው?
3. የቆንጂት መምህር የደነገጡት ለምንድን ነው?
4. በመጨረሻ መምህሩ ቆንጂትን እንዴት አበረታቷት?


ቃላት

በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. መፍጠር
2. መሳተፍ
3. መገረም
4. መደንገጥ
5. ማመስገን

መፃፍ

ቃሎቹን በማጣመር ሌሎች ቃሎችን ፃፉ።

ማዕድ	+		ምሳሌ፦ ማዕድ ቤት
ማረሚያ			
መኝታ			
ዳቦ			
ሥጋ			
ምግብ			

3ኛ ቀን

ማዳመጥ

የአካል ጉዳተኝነት

ለጥያቄው በቃላችሁ መልስ ስጡ።

የአካል ጉዳተኞች በምን በምን ስፖርታዊ ውድድሮች ሲሳተፉ አይታችኋል?

መነጠል


በምሳሌው መሠረት ነጥላችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፦ ተፈጠረ → ተ - ፈጠረ

1. ተወሰደ 2. ተቀነሰ 3. ተጨመረ 4. ተገረመ

ግለንባብ

ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች



በየትኛውም ትምህርትቤት ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች አሉ። ከእነሱም መካከል አካል ጉዳተኞች ይገኙባቸዋል። ለምሳሌ ዓይነስውሮች፣ መስማት የተሳናቸው ወይም ሌሎች አካላዊና አእምሯዊ ጉዳት የደረሰባቸው ተማሪዎች ሊጠቀሱ ይችላሉ።

"አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ምቹ ሁኔታ ካልተፈጠረላቸው ምን ችግር ይፈጠርባቸዋል?"

እነዚህ ተማሪዎች ምቹ ሁኔታ ካልተፈጠረላቸው በስተቀር በቂ እውቀት ለመገብየት ይቸገራሉ። ነገር ግን አስፈላጊ ቁሳቁስ ከተሟላላቸው ችሎታቸውን ማሳየት ይችላሉ። የትምህርት ተደራሽነትን ለማፋጠን ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች መለየትና ድጋፍ መስጠት የሁሉም ዜጋ ግዴታ ነው።

4ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

በምሳሌው መሠረት ቃላቱን መድቡ።

ማዳላት	ማግለል	ፍቅር መስጠት	ድጋፍ ማድረግ
ማራቅ	ልዩነት መፍጠር	ማክበር	

	ለሀገር ዕድገት	
	የሚጠቅሙ	የማይጠቅሙ
ምሳሌ →	ማክበር	ማዳላት

ቃላት

ቃላቱን በማቃረን አዛምዱ።

	“ሀ”		“ለ”
ለ	1. ማክበር	ሀ.	መከልከል
	2. ማግለል	ለ.	ማዋረድ
	3. መጥቀም	ሐ.	ማቅረብ
	4. መመረቅ	መ.	መርገም
	5. መስጠት	ሠ.	መጉዳት

መፃፍ

በጥያቄው ላይ ተወያይታችሁ መልሱን በፅሁፍ አቅርቡ።


አካል ጉዳተኞች የተለያዩ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ምን ምን ዓይነት ድጋፎች ያስፈልጓቸዋል?

25ኛ ሣምንት

1ኛ ቀን

ማዳመጥ

ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችና የሚሠሩባቸው ቁሶች



ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. ክራር 2. ዋሽንት 3. ከበሮ 4. ቃጭል

ማጣመር

ሀ. ቃላቱን ወደብዙ ቁጥር ለውጧቸው።

1. ማሲንቆ 2. ቃጭል 3. ፅናፅል 4. መለከት 5. ደወል

ለ. ፊደላቱን አጣምራችሁ ፃፉና አንብቡ።

ምሳሌ፦ የ - ዋ - ን - ዛ + እ - ን - ጨ - ት → የዋንዛ እንጨት

1. የ - ጥ - ድ + እ - ን - ጨ - ት
2. የ - ዝ - ግ - ባ + እ - ን - ጨ - ት

ግለንባብ

ባለዋሽንቱ



አንድ ምሽት ዋሽንት ተጫዋቹ ዋሽንቱን ይዞ የባህል ሙዚቃ ወደሚጫወትበት ቤት ሄደ። ታዳሚዎቹ ፊት ለፊት ተቀምጠው የዝግጅቱን መጀመር መጠባበቅ ያዙ። የባህል ሙዚቃ ተጫዋቾቹ ወደ መድረኩ ወጡ፤ መጫወትም ጀመሩ። ዋሽንት ተጫዋቹ መድረኩ ላይ በድንገት በመታመሙ ዋሽንቱ ከእጁ አምልጦ ወደቀ።

“ዋሽንት ተጫዋቹ የጣለው ዋሽንት ምን የሚሆን ይመስላችኋል?”

አጠገቡ የነበረው ጓደኛውም ሳያስተውል ዋሽንቱን ረገጠው። ዋሽንት ተጫዋቹም ህመሙ ሲሻለው የዋሽንቱን መሰበር አይቶ አዘነ። ጓደኛውም “እንኳን አንተን ተሻለህ እንጂ፣ ከባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ መሸጫ ቤት ሌላ ዋሽንት እንገዛለን” ብሎ አፅናናው።

2ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

በምንባቡ መሠረት ለጥያቄዎች ምላሽ ስጡ።

1. ባለዋሽንቱ መድረክ ላይ ከወጣ በኋላ ምን አደረገ?
2. ባለዋሽንቱ ያዘነው ለምንድን ነው?
3. ጓደኛው ባለዋሽንቱን ያጽናናው ምን በማለት ነው?
4. የዋሽንት ድምፅ ስትሰሙ ምን ዓይነት ስሜት ይሰማችኋል?

ቃላት

ባዳመጣችሁት መሠረት የባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችን ስያሜ መድቡ።

	ባህላዊ የምት የሙዚቃ መሣሪያዎች	ባህላዊ የትንፋሽ የሙዚቃ መሣሪያዎች	ባህላዊ የክር የሙዚቃ መሣሪያዎች
ምሳሌ፡-	ነጋሪት	ዋሽንት	በገና

መፃፍ

ለጥያቄዎቹ ትክክለኛውን መልሶች ፃፉ።

1. የክር ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችን ለማዘጋጀት ምን ምን ነገሮች ያስፈልጋሉ?
2. ደስ ያላችሁን አንድ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያ ሥዕል ሳሉ።

3ኛ ቀን

ማዳመጥ

ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችና የሚሠሩባቸው ቁሶች

ቃላት

በምሳሌው መሠረት ቃላቱን መድቡ።

ነጋሪት	ደወል	ቃጭል
ከበሮ	አታሞ	ፅናፅል

	ከቆዳ የሚሠሩ	ከብረት የሚሠሩ
ምሳሌ፦	ከበሮ	ቃጭል

ማጣመር


በምሳሌው መሰረት አጣምራችሁ አንብቡ።

ምሳሌ፦ ቆዳ - ዎች → ቆዳዎች

1. ቀዳዳ - ዎች
2. ጣውላ - ዎች

ግለንባብ

የማሲንቆ አዘገጃጀት



ማሲንቆ ከክር ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች መካከል አንዱ ነው። ማሲንቆ ለማዘጋጀት ብዙ የፈረስ ጭራዎች አንድ ላይ ይሸረባሉ። ከዚያ በኋላ ሣጥን መሰል ነገር ከጣውላ ይዘጋጃል፤ ድምፁንም ለማጉላት በፍየል ቆዳ ይሸፈናል። በተጨማሪም በሳጥኑ በአንደኛው ማዕዘን ውስጥ

ቁልቁል አንድ ቋሚ እንጨት ይገባል። በቋሚው እንጨት ላይ የፈረስ ጭራው ይወጠራል። ሌላ ደጋን የመሰለ እንጨትም ይዘጋጃል። በዚህ እንጨት ላይ የፈረስ ጭራ ይወጠራል።

"የፈረሱ ጭራ ለምን የሚያገለግል ይመስላችኋል?"

ሁለቱን የተወጠሩ የፈረስ ጭራዎች ርስበርስ በመገዘገዝ ድምፅ እንዲወጣ ይደረጋል።

4ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ለጥያቄዎቹ በምንባቡ መሠረት መልስ ፃፉ።

1. ማሲንቆ ምን ዓይነት መሣሪያ ነው?
2. የፈረስ ጭራ ለምን ያገለግላል?
3. የፍየል ቆዳ ለምን ያገለግላል?

ቃላት

በምሳሌው መሠረት ከ"ለ" ወደ"ሀ" አዛምዱ።

	"ሀ"	"ለ"
ሠ	1. ክራር	ሀ. ይመታል
	2. ዋሽንት	ለ. ይጎሰማል
	3. ደወል	ሐ. ይነፋል
	4. ማሲንቆ	መ. ይደወላል
	5. ነጋሪት	ሠ. ይደረደራል



መፃፍ

ሥርዓተነጥቦቹን በመምረጥ በተገቢ ቦታ ፃፉ።

፣	።	?	፤

1. ክራር ማሲንቆና በገና የክር የሙዚቃ መሣሪያዎች ናቸው
2. ከበሮ ለመስራት የዋንዛ እንጨት ይጠረባል የከብት ቆዳ ይሩቃል
3. ምን ዓይነት የሙዚቃ መሣሪያ ትወዳላችሁ
4. ከበደ የፈረስ ጭራዎችን ሰበሰበ ሸረበ የጣውላ እንጨትም አዘጋጀ

1ኛ ቀን

ማዳመጥ

የሠርግ ዘፈኖች



ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ::

1. አሳደጉ
2. አቆላመጡ
3. አደመቁ
4. ዘፈኑ

ማጣመር

በምሳሌው መሠረት የሌሎችን ቃሎች ቅርፅ ለውጡ::

ምሳሌ፡-	ዘናጭ →	ዘናጩ →	ዘናጯ
1.	ዘፋኝ →	_____ →	_____
2.	አልቃሽ →	_____ →	_____
3.	አዛኝ →	_____ →	_____

ግለንባብ

ለቀስተኛዋ

ሠፈሩ ያለወትሮው በጩኸት ታምሷል:: የአካባቢው ሰዎች ጩኸት ወደሰሙበት አቅጣጫ ይሮጣሉ:: እኔም ከሚጮኽበት ቦታ ደረስኩ:: አንዲት ትልቅ ሴት መሃል ሆነው ሌሎቹ ደግሞ ዙሪያውን ከበው ያለቅሳሉ:: መሃል የቆሙት ለቀስተኛዋም፣



“እጇን አትቅበሩት ይቁም እንደአገዳ፣
ሽኝታበታለች ብዙ ብዙ እንግዳ።
እሷን አትቅበሯት ካንገቷ በላይ፣
ሲወጡ ሲገቡ ልጆቿን እንድታይ”

በማለት በልጃቸው ሞት በሀዘን በተሰበረ መንፈስ ይንሰቀሰቃሉ። በዙሪያው የከበበው ሁሉም ሰው ይጮሃል፤ ያለቅሳል። እኔም ሚቿን ባላውቃትም ሁኔታው አስለቀሰኝ።

2ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎቹን በምንባቡ መሠረት መልሱ።

1. ሠፈሩ በጩኸት የታመሰው ለምንድን ነው?
2. ሰዎቹስ የሚሮጡት ለምንድን ነው?
3. ተራኪው ያለቀሰው ለምንድን ነው?
4. በእናንተ አካባቢ ሰው ሲሞት በለቅሶ ሥነሥርዓቱ ላይ ምን ምን ይደረጋል?

ቃላት

ቃላቱን በማመሳሰል አዛምዱ።

	“ሀ”	“ለ”
መ	1. ዙሪያ	ሀ. ትንሽ
	2. ያማረ	ለ. ጭማሪ
	3. ጥቂት	ሐ. ሁልጊዜ
	4. ድጋሚ	መ. ክብ
	5. ዘወትር	ሠ. የተዋበ

መሳፍ

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን በደብተራችሁ ፃፉ። አስፈላጊ ሥርዓተነጥቦችንም ተጠቀሙ።

3ኛ ቀን

ማዳመጥ

የሠርግ ዘፈኖች

ቃላት

በምሳሌው መሠረት ሌሎችን አሟልታችሁ ፃፉ።

ምሳሌ፡- ጉድጓድ ይቆፈራል።

1. ለቅሶ
2. እርሻ
3. ጉልጓሎ

ማጣመር

በብዙ ቁጥር ፃፉ።

ምሳሌ፦ በዓል → በዓሎች

1. ዘፈን
2. ባህል
3. ድል
4. ሰርግ

ግለንባብ

ባህላዊ ዘፈኖች



ሰዎች ደስታቸውን ለመግለፅ ባህላዊ ዘፈኖችን ይዘፍናሉ።

"ባህላዊ ዘፈኖች መቼ መቼ ይዘፈናሉ?"

በሠርግ፣ በሥራ፣ በዘመን መለወጫ በዓልና በመሳሰሉት ባህላዊ ዘፈኖችን መዝፈን የተለመደ ነው። ለምሳሌ በሰርግ ጊዜ ሙሽራዎችንና ወላጆቻቸውን ለማድነቅና ለማሞገስ ይዘፈናል። በሥራ ጊዜ ደግሞ በተለይ እርሻ ሲታረስ፣ ጉልጓሎ ሲጎለጎል፣ እህል ሲበራይ (ሲወቃ) ወዘተ. አርሶአደሮች ብርታት እንዲያገኙ ይዘፍናሉ። በበዓላት ቀናትም በዓላቱን የሚገልፁ ባህላዊ ዘፈኖች ይዘፍናሉ። ባህላዊ ዘፈኖች የህዝብ ቃላዊ ሃብቶች ናቸው። በአብዛኛው ክንዋኔዎች ሲከናወኑ የክንዋኔዎቹ ማድመቂያዎች ሆነው ያገለግላሉ።

4ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት መልሱ።

1. ባህላዊ ዘፈኖች የት የት ይዘፈናሉ?
2. አርሶአደሮች በሥራ ወቅት የሚዘፍኑት ለምንድን ነው?
3. ከባህላዊ ዘፈኖች የአንዱን አዝማች ፃፉና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

ቃላት

ክቦቹን በተገቢ ቃላት ሙሉ።



መፃፍ

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን በደብተራችሁ ፃፉ።

1ኛ ቀን



ማዳመጥ

የኢድአልፊጥር በዓል አከባበር



ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. ገንፎ 2. ዳቦ ቆሎ 3. ያም 4. ፀሎት 5. ምግብ



ማጣመር

የተጓደሉ ፊደላትን በማሟላት ቃላት መሥርቱ።

ምሳሌ፦ በ - ል → በዓል

1. ጨ - ረ 2. ዓ - ት 3. ገ - ር 4. አ - በ



ግለንባብ

ሐሊማ በአረፋ ዋዜማ

ሐሊማ ጓደኞቿን ይዛ እየሮጠች ወደቤቷ ገባች። የቤቱ ዕቃዎች ሳሎኑን ሞልተውታል። ሐሊማ "አበበ፣ ደብሪቱ እዚህ ቆዩኝ" አለቻቸውና ዕቃዎቹ እንዳይሰበሩ እየተጠነቀቀች መራመድ ጀመረች። "እማዬ! እማዬ!" ብላ ተጣራች። አባቷ ከወደጓሮ ብቅ አሉ። "ምን ሆነሻል?" አሏት።



"አባቷ ሐሊማን፣ "ምን ሆነሻል?" ብለው ሲጠይቋት ምን የምትመልስ ይመስላችኋል?"

“አይ! እኔ ከጓደኞቼ ጋር ላዘጋጅ የነበረውን እቃ ምስቅልቅሉን ስላወጣችሁብኝ ተናድጄ ነው” አለቻቸው። “አይ ልጄ፣ በአረፋ በዓል ሁላችንም ተጋግዘን ቤታችንን ዝግጁ ማድረግ አለብን” አሏት። “እሱማ ትክክል ነህ፤ እኔም እኮ ይህን አስቤ ጓደኞቼን ይዣቸው መጥቻለሁ” አለች ሐሊማ። አባቷም፣ “ጎሽ የእኔ ልጅ! መተጋገዝ እንደዚህ ነው፤ አንቺ ደግሞ የእነሱ በዓላት ገና፣ ጥምቀትና ፋሲካ ሲከበሩ በሥራ ታግዣቸዋለሽ” አሏት።

2ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት መልሱ።

1. እነሐሊማ የሚያከብሩት በዓል ምን በመባል ይታወቃል?
2. ሐሊማ የተናደደችው ለምንድን ነው?
3. የሐሊማ ጓደኞች እነማን ናቸው?
4. የእነደብሪቱ በዓላት ምን ምን በመባል ይታወቃሉ?

ቃላት

በነጠላ ቁጥር ፃፉ።

ምሳሌ፦ ጌጦች → ጌጥ

1. ሴቶች 2. አማኞች 3. ታቦቶች 4. ገጠሮች

መፃፍ

በእስልምና ኃይማኖት በዓላት የሚዘጋጁ የምግብና የመጠጥ ዓይነቶችን ፃፉ።

ምግብ	መጠጥ
ዶሮ ወጥ	አብሽ

3ኛ ቀን



ማዳመጥ

የኢድአልፊጥር በዓል አከባበር



ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. ጎረቤት　　2. ፍራፍሬ　　3. ሶላት　　4. መዝናናት



ማጣመር

ቃላትን ወደብዙ ቁጥር ለውጡ።

1. ጎረቤት → ጎረቤቶች

1. ካህን　　2. ቄስ　　3. ተከታይ　　4. ሼህ



ግለንባብ

የጥምቀት በዓል አከባበር

የጥምቀት በዓል በየዓመቱ ጥር አሥራአንድ ቀን በደመቀ ሁኔታ ይከበራል።

"በአዲስ አበባ ከተማ የሚኖሩ አብዛኛዎቹ ሴቶች ምን አይነት ልብስ ይለብሳሉ?"

በአዲስ አበባ ከተማ የሚኖሩ አብዛኛዎቹ ሴቶች ፅአዳ የአገር ባህል ቀሚስ ለብሰው ያጌጣሉ። በከተራ (በዋዜማው ዕለት) የየቤተክርስቲያናቱ ታቦቶች ታጅበው ወደ ጃን ሜዳና ወደተዘጋጀላቸው ሌሎች ማደሪያ ስፍራዎች ይሄዳሉ። ታቦቶቹ በአማኞች፣ በካህናትና በቀሳውስት ይታጀባሉ። ከዚያ በኋላ ሌሊቱን በሙሉ ፀሎት ሲደረግ ያድራል። ሲነጋ በጧት አማኞች ይጠመቃሉ። ከዚያም ረፈድ ሲል ካህናት እያሸበሸቡ፣ መዘምራን እየዘመሩ፣ ወጣቶች እየጨፈሩ ታቦታቱን አጅበው ወደየቤተክርስቲያኖቻቸው ያስገባሉ።

4ኛ ቀን


አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

1. የከተራ (የጥምቀት ዋዜማ) እለት ታቦቶች ወደየት ይሄዳሉ?
2. በጥምቀት በዓል በአዲስ አበባ ከተማ የሚኖሩ አብዛኛዎቹ ሴቶች በምን አይነት ልብስ ያጌጣሉ?
3. የጥምቀት በዓል ሲከበር አይታችሁ ታውቃላችሁ?
   ምን ምን ነገሮችን አይታችኋል?

ቃላት

ሳጥኖቹን በተገቢ ቃላት አሟሉ።



መፃፍ

የድርጊት ቅደምተከተሎችን በምንባቡ መሠረት ፃፉ።

የጥምቀት በዓል አከባበር

መጀመሪያ፦ ታቦታት ወደ ጃን ሜዳ ወይም ወደ ተዘጋጀላቸው ሌሎች ማደሪያ ስፍራዎች ይወርዳሉ።

በመቀጠል፦ የእምነቱ ተከታዮች ሲፀልዩ ያድራሉ።

ከዚያ በኋላ፦ _____ ።

በመቀጠል፦ _____ ።

በመጨረሻ፦ _____ ።

1ኛ ቀን

ማዳመጥ



የአርበኞች ተጋድሎ

ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. ዘመቱ 2. ተዋጉ 3. ተፋለሙ 4. ተሸነፉ 5. ነፃ አወጡ

ማጣመር

በምሳሌው መሠረት ሌሎች ቃላት መስርቱ።

ሠራተኛ → ሠራተኞች

1. አርበኛ 2. ሰልፈኛ 3. ፈረሰኛ

ግለንባብ

ግንቦት 20

እለቱ የግንቦት 20 በዓል የሚከበርበት ነው። ትምህርትቤቱ በተለያዩ ሰንደቅ ዓላማዎች አሸብርቋል። ተማሪዎች የደንብ ልብሳቸውን ለብሰዋል። መፈክሮችንና ትንንሽ ሰንደቅ ዓላማዎችን ይዘዋል። መምህሮችም ተማሪዎቻቸውን ለማሰለፍ ላይታች ይላሉ። ተማሪዎቹ ተሰለፉ።



"ተማሪዎች ከተሰለፉ በኋላ ምን የሚያደርጉ ይመስላችኋል?"

መዝሙራቸውንም እየዘመሩ ወደ መስቀል አደባባይ ተመሙ። "ነፃነት ያኮራል ሃገር ያስከብራል፤" የሚለው የመዝሙራቸው አዝማች ጎልቶ ይሰማል። መስቀል አደባባይ ደረሱ። በአራቱ ማዕዘናት ህዝቡ ወደ አደባባዩ ነጎደ፤ ፈረሰኞችም ፈረሶቻቸውን አሳምረውና አስጊጠው እየጋለቡ ለበዓሉ ድምቀት ሰጡት።

2ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት መልሱ።

1. ትምህርት ቤቱ ያሸበረቀው ለምንድን ነው?
2. የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ምን ምን ዓይነት ቀለማት አሉት?
3. በእናንተ ትምህርትቤት የድል በዓላትን እንዴት ታከብራላችሁ?

ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. ሰልፍ
2. መዝሙር
3. በዓል

መሳፍ

ወደሰልፍ ስትሄዱ ምን ምን ነገሮችን ትይዛላችሁ? በቡድን ተወያዩና ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

3ኛ ቀን




ማዳመጥ

የአርበኞች ተጋድሎ



ቃላት

የኢትዮጵያ ብሄራዊ በዓሎችን ዘርዝራችሁ ፃፉ::





ማጣመር

በአንስታይና በብዙ ቁጥር ፃፉ::

ተባዕታይ	አንስታይ	ብዙ
አሸነፈ	_____	_____
ተዋጋ	_____	_____
መራ	_____	_____
ወረረ	_____	_____



ግለንባብ

ህዝባዊ በዓላት

በኢትዮጵያ ብዙ ህዝባዊ በዓላት አሉ:: እነዚህ በዓላት ብሔራዊ በዓላት ሊሆኑ ይችላሉ:: በዓመት አንድ ጊዜ ይከበራሉ::

"የአድዋ ድል በዓል መቼ ይከበራል?"

የአድዋ ድል በዓል የካቲት 23 ቀን ይከበራል። የነፃነት ቀን ደግሞ ሚያዝያ 27 ቀን ይከበራል። ሌላው የህዝብ በዓል ሚያዝያ 23 የሚከበረው የሠራተኞች ቀን ነው። በተጨማሪም ግንቦት 20 ቀን ደርግ ከስልጣን የወረደበት ሲሆን፣ መስከረም 1 ቀን ደግሞ የዘመን መለወጫ በዓል ነው። ሁሉም በዓላት በሚከበሩበት ዕለት መሥሪያ ቤቶች ተዘግተው ይውላሉ።

4ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት መልሱ።

1. ብሔራዊ በዓላት የምንላቸውን ፃፉ?
2. የግንቦት 20 በዓል የሚከበረው ለምንድን ነው?
3. የነፃነት ቀን በዓል መቼ ይከበራል?

ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ።


1. ዘመተ
2. ተዋጋ
3. አሸነፈ
4. ተመለሰ
5. ወረረ

መፃፍ

ጥያቄዎችን በጽሑፍ መልሱ።

1. ከምታውቋቸው መፈክሮች መካከል ሁለቱን ፃፉ።
2. ከምታውቋቸው የድል መዝሙሮች መካከል የአንዱን አዝማች ጽፋችሁ አንብቡ።

1ኛ ቀን



ማዳመጥ

የፋሲካ በዓል

ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ::

1. ባቄላ
2. ጉልባን
3. ቁርጥ
4. ክትፎ

መነጠል

በነጠላ ቁጥር ፃፉ::

1. መጠጦች → መጠጥ
3. ዘመዶች → _____
2. ቅመሞች → _____
4. ወዳጆች → _____

ግለንባብ

“የፈሰሰ ውኃ...”



የዶሮ ወጡና የበጉ ሥጋ ጥብስ ሽታ ሆድን ይበረብራል:: አይብ፣ እርጎና በቅቤ የረሰረሰ ክትፎ ተደርድሯል:: ጠላውና ጠጁ በጠርሙስና በብርሌ ተንቆርቁሮ ቀርቧል:: ወይዘሮ ዘርፌ እንግዶቻቸው ዘግይተውባቸው ወጣ ገባ ይላሉ:: ድንገት ከወደኋላቸው የኳኳታ ድምፅ ሰሙ::

“ወይዘሮ ዘርፌ የሰሙት የኳኳታ ድምፅ ምን ይሆናል ብላችሁ ታስባላችሁ?”

አንድ ድመት እመር ብላ ባጠገባቸው አለፈች። ዞር ሲሉ ልጃቸው ሰይፉ ዱላ ይዞ ሲሮጥ ተጋጩ። “ምንድን ነው ጉዱ?” አሉ ወይዘሮ ዘርፌ። “እማዬ እይው እስኪ!” ብሎ አሳያቸው። በጠረጴዛ ላይ ያለው እርጎ ተደፍቷል። “በል ልጄ የፈሰሰ ውኃ አይታፈስም፤ ሌላ እናቀርባለን” አሉትና ተያይዘው ወደጓዳ ገቡ።

2ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ለጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት መልስ ስጡ።

1. ከተዘጋጁት ምግቦች ውስጥ የተደፋው ምንድን ነው?
2. ወይዘሮ ዘርፌ ወጣገባ የሚሉት ለምንድን ነው?
3. እናንተ ሰይፉን ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር?
4. “የፈሰሰ ውኃ አይታፈስም” ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?


ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. ጠላ
2. ጠጅ
3. ቅቤ
4. እርጎ

መፃፍ

ሳጥኖችን በምሳሌው መሠረት አሟሉ።




3ኛ ቀን

ማዳመጥ

የፋሲካ በዓል

ቃላት

የወጥ ዓይነቶችን በክቦቹ ውስጥ ዘርዝሩ።



ማጣመር


ፊደሉንና ቃላቱን በማጣመር ቃላት መስርቱ።

ምሳሌ፦ ተ _ ለቀቀ → ተለቀቀ

ተ _ በላ　　ተ _ ገደፈ　　ተ _ ጠጣ

ግለንባብ

የዶሮ ወጥ አሠራር



ከበዓላት ምግቦች አንዱ የዶሮ ወጥ ነው። የዶሮ ወጥ አሰራር የራሱ ሂደት አለው። በመጀመሪያ ዶሮ ያስፈልጋል። ከዚያ በኋላ ውሃ ይፈላል። ዶሮው በሰላ ቢላዋ ይታረዳል። ትልልቅ ላባዎች ይነጨና የቀሩት ላባዎች ከቆዳው እንዲላቀቁ የፈላ ውሃ ይጨመርበታል። ጥቂት ቆይቶ ላባውን ከቆዳው በመንጨት እንዲለቅ ይደረጋል።

"በዶሮ ወጥ አሠራር ሂደት የዶሮው ላባ ከቆዳው ላይ በመንጨት ከተላቀቀ በኋላ ምን ይደረጋል?"

ከዚያም በቀሰም ይነፋና ወረቀት በማቀጣጠል ይለበለባል። ከዚያ በኋላ በደንብ ይታጠብና ይበለታል። የተበለተው የዶሮ ሥጋ በሎሚና በጨው ለጥቂት ጊዜ ይዘፈዘፋል። እንደገና ሙልጭ ተደርጎ በደንብ

ይታጠባል። የተከተፈው ሽንኩርት ይጣድና ይበስላል። ዘይት፣ በርበሬ ይገባበታል። በደንብ ከተቁላላ በኋላ የዶሮው ሥጋ ተጨምሮ ይበስላል። ከዚያም ቅቤ፣ ቅመማቅመምና ተቀቅለው የተላጡ እንቁላሎችን በመጨመርና የጨውንም ልክ በማስተካከል ይወጣል።

4ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት


ለጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልስ ስጡ።

1. ላባው ከተነጨ በኋላ ዶሮው ወረቀት በማቀጣጠል የሚለበለበው ለምንድን ነው?
2. ቀጥሎ የቀረበውን የዶሮ ወጥ አሠራር ቅደምተከተል አስተካክላችሁ ፃፉ።

ይሠራል	ይለበለባል	ይታረዳል	ይገዛል
ይጨመራል	ይበስላል	ይዘፈዘፋል	

ቃላት

የመጠጥ ዓይነቶችን በሳጥኖቹ ውስጥ ፃፉ።



መፃፍ

ሥርዓተነጥቦችን በተገቢ ቦታ ፃፉ።

፣	?	፤	::

1. ለዓመት በዓል ዶሮ ይገዛል ይታረድና ይሠራል
2. ገበያ ሄጄ ሽንኩርት ዘይትና በርበሬ ገዛሁ
3. ዶሮ ወጥ ለመሥራት ምን ምን ነገሮች ያስፈልጋሉ

1ኛ ቀን

ማዳመጥ

ቀረርቶና ፉከራ



ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ።

ምሳሌ፦ ስሜት → ቃላዊ ሀብቶች ስሜትን ይቀሰቅሳሉ።

1. ቀረርቶ
2. ፉከራ
3. ዜማ
4. ግጥም

ማጣመር

“አስ-” የሚለውን ቅጥያ ከቃላቱ አጣምራችሁ ፃፉ።

ምሳሌ፦ አስ + ጨነቀ → አስጨነቀ

1. አስ + ተማረ
2. አስ + በጠረ
3. አስ + ፎከረ
4. አስ + ለበሰ

ግለንባብ

እነአብርሃም በቡሄ በዓል

የቡሄ በዓል የሚከበርበት እለት ነበር። እነአብርሃም፣

“ሆያ ሆዬ፣ ሆያ ሆዬ
የእኔማ አባት የሰጡኝ ሙክት
ከግንባሩ ላይ አለው ምልክት።”



የሚሉትንና ሌሎችንም ግጥሞች እየገጠሙ ሲጨፍሩ አመሹ። የሰፈር ሰዎችም እየመረቁ ዳቦ፣ ብር፣ ሳንቲም ሰጧቸው። ጓደኛቸው ግን አልነበረም። ወደቤቱ ሄዱ። “ምንሆነህ ነው የቀረኸው?” አሉት። “ምን ለብሼ ልውጣ?” አላቸው ፤እንባ እየተናነቀው። እነአብርሃምም ተመካክሩና ባገኙት ገንዘብ በማግስቱ ልብስ ገዙለት። ጓደኛቸውም አቅፎ ሳማቸው።

2ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት መልሱ።

1. ታሪኩ ስለእነማን ይናገራል?
2. እነአብርሃም ለጓደኛቸው ምን አደረጉለት?
3. የእነአብርሃም ጓደኛ ምን ዓይነት ኑሮ የሚኖር ይመስላችኋል?

ቃላት

ቃላትን ከአባባላቸው ጋር አዛምዱ።

“ሀ”	“ለ”
1. ዘፈን	ሀ. ይወረዳል
2. ቀረርቶ	ለ. ይሸለላል
3. ፉከራ	ሐ. ይጨፈራል
4. ሽለላ	መ. ይቅራራል
5. እስክስታ	ሠ. ይፎክራል
6. ጭፈራ	ረ. ይዘፈናል

መፃፍ

ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. ጨፈረ
2. ሰጠ
3. መረቀ
4. መከረ

3ኛ ቀን

ማዳመጥ

ቀረርቶና ፉከራ

ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ።

1. ቃላዊ ሃብቶች የምንላቸው ምን ምን ናቸው?
2. ሰዎች ሲያቅራሩ ምን ዓይነት እንቅስቃሴዎችን ያደርጋሉ?
3. ሰዎች ሲፎክሩስ በምን ዓይነት እንቅስቃሴ ነው?
4. የፉከራና የቀረርቶ ዜማዎችን ከእንቅስቃሴ ጋር በክፍል ውስጥ አሳዩ።

ማጣመር

ወደብዙ ቁጥር ለውጡ።

ምሳሌ 1፦ ግጥም → ግጥሞች

1. ክምር → _____
2. ሙክት → _____
3. ምልክት → _____
4. አባት → _____

ምሳሌ 2፦ ፉከራ → ፉከራዎች

1. አውድማ → _____
2. አበጣሪ → _____
3. እርሻ → _____
4. ቆፋሪ → _____

ግለንባብ

እስክስታ

እስክስታ ባህላዊ የጭፈራ አይነት ነው። በተለይም በአማራ ክልል የተለመደ ውዝዋዜ ነው። ሰዎች ባህላዊ ዘፈኖችን ሲዘፍኑ ወገባቸውን በነጠላ ሽብ ያደርጋሉ። ትከሻቸውን፣ ወገባቸውንና አንገታቸውን በማንቀሳቀስ እስክስታ ይወርዳሉ። የእስክስታ አወራረዱ እንደየአካባቢው ይለያያል።



"የየት አካባቢ እስክስታ ታውቃላችሁ?"

የጎንደር፣ የጐጃም፣ የምንጃር፣ የወሎ እስክስታ በመባልም ይገለፃል። በሠርግ ቦታና በበዓላት ጊዜ የተለመደ ነው። ባህላዊ ውዝዋዜዎች ሁሉ በእስክስታ የታጀቡ ናቸው። ስለዚህ እስክስታ ሰውነትንና አእምሮን ዘና ያደርጋል። የአካል ጥንካሬንም ይሰጣል።

4ኛ ቀን

አንብቦ መረዳት

ለጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ በቃላችሁ ስጡ።

1. የምንባቡን የመጀመሪያ ዓረፍተነገር ለመምህራችሁ ንገሩ።
2. ሰዎች እስክስታ ሲወርዱ ወገባቸውን በምን ሸብ ያደርጋሉ?
3. ባህላዊ ውዝዋዜዎች በምን የታጀቡ ናቸው?
4. እስክስታ ከመዝናናት ሌላ ምን ጥቅም ይሰጣል?
5. ሌሎች የምታውቋቸውን ባህላዊ ውዝዋዜዎች ግለፁ።

ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. ተወላወለ
2. ጨፈረች
3. አበጠረ
4. ፎከረች

መፃፍ

በምሳሌው መሠረት አሟልታችሁ ፃፉ።

